በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በመንግስት ግዥ እና ንብረት ባለስልጣን

የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝ እና የነዳጅ አጠቃቀም ውጤታማነት

በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

Office of the Federal Auditor General

ሚያዝያ 2017 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ማጠቃለያ (Executive Summery) i
ክፍል አንድ 5
መግቢያ 5
የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን አመሠራረት 5
የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ራዕይ፣ ተልዕኮ፡ 5
ራዕይ (Vission) 5
2. በ2017 ዓ.ም በአፍሪካ ተፎካካሪ የመንግስት የግዥና ንብረት ተቆጣጣሪ ተቋም ሆኖ መገኘት፤ .5
ተልዕኮ (Mission) 5
ዓላማ (Objective) 6
የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ስልጣንና ተግባር 6
የባለስልጣን መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል አደረጃጀት 10
ድርጅታዊ መዋቅር 10
የሰው ኃይል 10
የባለስልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ 10
ኦዲቱ አላማ 11
ኦዲቱ አካባቢ (Audit Area) 12
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) 12
የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) 12
የኦዲት ወሰንና ዘዴ 13
የኦዲቱ ወሰን 13
የኦዲቱ ዘዴ 13
የአሰራር ስርዓት መግለጫ 14
/Process description/ 14
ክፍል ሁለት 15
ግኝቶች 15
የተሽከርካሪ አያያዝ፣ ስምሪት እና የነዳጅ አጠቃቀም የአሰራር ሥርዓት ተግባራዊ እና ወቅታዊ መደረጉን በተመለከተ 15
ለበላይ ኃላፊዎች በህግ በተፈቀደው መሰረት ተሽከርካሪዎች ስለመመደቡንና ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጡን በተመለከተ፡- 18
ተሽከርካሪዎች፣ ነዳጅ እና ቅባት፣ በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፡ 23
የነዳጅ እና የተሽከርካሪ አጠቃቀም ግምገማና ግብረ-መልስ የሚሰጥ መሆኑን በተመለከተ፡- 25

የፌደራል መ/ቤቶች የነዳጅና የጥገና እቃዎች ወጪ ወርሃዊ ሪፖርት እንዲያቀርቡ መድረጉን በተመለከተ፡- 27
የተሸከርካሪዎችና ነዳጅ አጠቃቀም የህጋዊነት ኦዲት መድረጉንና ሪፖርት መቅረቡን በተመለከተ፡- 29
የተሸከርካሪ አጠቃቀምን መቆጣጠርያ የሥምሪት አስተዳደር (Fleet Management ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፡- 31
ተሸከርካሪዎች ለእያንዳንዳቸው የህይወት ታሪክ መዝገብ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ፡ 34
በተሸከርካሪ ጥገና ወቅት የተለወጡ እቃዎች በአግባቡ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ መደረጋቸውን በተመለከተ፡ 35
የፌዴራል ተቋማት የተሸከርካሪዎች ዓመታዊ የመረጃ ሪፖርት ማቅረባቸውን በተመለከተ 37
የተሸከርካሪዎችን የጥገና አገልግሎት ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን ማድረጉን በተመለከተ፤ 39
የተሸከርካሪዎችን ሥምሪትና የነዳጅ አጠቃቀም ጥናት መድረጉን በተመለከተ 43
በተሸከርካሪና ነዳጅ አጠቃቀም አስተዳደርን የቅንጅት ስርዓት መዘርጋቱ በተመለከተ፡- 45
በተሸከርካሪ እና ነዳጅ አጠቃቀም የመረጃ ሥርዓት እና መደበኛና ጠንካራ የመረጃ ልውውጥ መኖሩን በተመለከተ፡- 46
ክፍል ሶስት 49
መደምደሚያ 49
ክፍል አራት 52
የማሻሻያ ሃሣቦች 52
አባሪ- 1፡ የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) i
አባሪ 2: የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ድርጅታዊ መዋቅር v
አባሪ. 3 የመንግስት ግዥና ንብረት ማሻሻያና አቅም ግንባታ ስራ አስፈጻሚ ተግባር እና ኃላፊነት vi
አባሪ.4 በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ የፌደራል መ/ቤቶች ለበላይና ለከፍተኛ ኃላፊዎች ተሸከርካሪና ነዳጅ ከተፈቀደላቸው ውጪ የተመደበ ስለመሆኑ የሚያሳዩ 3 ሰንጠረዦች፡- vii
አባሪ.5 ለባለሥልጣኑ መረጃ የማይልኩና የኖራማላይዜሽን ልኬት የሚያከናውኑ ተቋማት xvii
አባሪ .6 ባለስልጣን መ/ቤቱ በፌደራል መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም እና የተሸከርካሪ ስምሪትና አያያዝ ግምገማና ግብረ-መልስ የሚሰጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ ያሉ ክፍተቶች ለማሳያ የሚሆን፡- xxiv
❖ አልፎ አልፎ የበላይ ኃላፊዎች የነዳጅ ወርሃዊ ሪፖርት በሚልኩ ተቋማት ለምሳሌ የኢትዮጵያ አእምራዊ ንብረት ባለስልጣን የምክትል ዋና ዳይሬክተር ተሸከርካሪ የሀምሌ ወር /2015 የተቀዳ ነዳጅ 511 ሊትር ነዳጅ የተቀዳ ሲሆን የጓዘው ኪ.ሜ ያልተገለፀ መሆኑ፣ ታርጋ ቁጥር 4-20345 የመስከረም/2016 ዓ.ም ተሸከርካሪ 370 ሊትር፣ የጥቅምት/2016 ዓ.ም ተሸከርካሪ 547 ሊትር፣ መቀዳቱ፣ የህዳር/2016 ዓ.ም ተሸከርካሪ 300 ሊትር፣ የታህሳስና ጥር/2016 ዓ.ም ተሸከርካሪ 496 ሊትር ቢቀዳለትም በመስክ ስራ ነው አይደለም የሚል ልተገለፀ መሆኑ፤ xxiv

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

❖ የኢትዮጲያ ስታስቲክስ አገልግሎት የታርጋ በህዳር/2016 ዓ.ም ቁጥር 4-11088፣ 4-18684፣ 4-32747፣ 4-25261፣ 4-18683፣ 4-11075፣ 4-15380፣ 4-16168፣ 4-32829፣ 4-15094፣ 4-11100፣ 4-15087፣ 4-26574፣ 4-11077፣ 4-16165፣ 4-18332፣ 4-11096፣ 4-16168 እና በጥር /2016 12 ተሽከርካሪዎች በተመሳሳይ ምንያህል ነዳጅ እንደተቀዳላቸውና ምን ያህል ኪ.ሜ እንደተጓዙ የሚገልጽ ነገር የሌለ መሆኑ፤ xxiv

❖ በኢትዮጲያ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን ከሚያዚያ - ግንቦት /2015 የነዳጅ ሪፖርት፡- 4-18787 በ2 ወር 515.95 ሊትር፤ 4-14784 በ 2ወር 863.67 ሊትር፤ 4-22171 በ 2 ወር 992.37፤ 4-14013 በ 2 ወር 768.88፤ 4-17201 በ 2 ወር የተቀዳው ነዳጅ 740.30 ሊትር ሲሆን በመስክ ነው አይደለም የሚል ገለፃ አለመደረጉ፤ xxiv

❖ የኢትዮጲያ ማሪታይም ባለስልጣን የመጋቢት፣ ግንቦት፣ ሰኔ፣ ሃምሌና ነሃሴ /2015 ዓ.ም የነዳጅ ሪፖርት፡ 4-21084- 576.5 ሊትር እና 354.15.፤ 4-13057 የተቀዳው ነዳጅ 275.76 እንዲሁም 29 ተሽከርካሪዎች እንዳሉት በደብዳቤ ቁጥር ከ70/ማባ88/11/15 በቀን ሀምሌ 5/2015 ዓ.ም ቢያሳውቅም ወርሀዊ የነዳጅ አጠቃቀም ሪፖርት የተላከው የ 7 ተሽከርካሪ ብቻ መሆኑ፤ xxv

❖ የስነምግባር እና ሙስና ኮሚሽን ባስጥ ማስታወሻ በ5/2/2016 ከትራንስፖርት ስምሪት ስራ ክፍል ለኮሚሽን ጽ/ቤት ኀላፊ የተፃፈ አለአግባብ ስለተቀዳ ነዳጅ ማለትም ናፍጣ1,398.75 ሊትር ዋጋው 111,550.31 ብር (ለሰሌዳ ቁጥር 4-14624፣ 4-14621፣ 4-14622፣ ፌሪ ካርድ)፤ ቤንዚን 410.18 ሊትር ዋጋው 31,836.5 ብር ለሰሌዳ ቁጥር 4-30608 እና 4-30083 የተቀዳላቸው መሆኑ ይህ የሆነበት ተሽከርካሪዎቹ በጋራዥ ቆሞ እያሉ ባልተፈቀደ መንገድ በቀን ሁለት ጊዜ በመቅዳት በገንዘብ 143, 386.82 ወጪ ተደርጎ እርምጃ ስለመወሰዱ የሚያሳይ ማስረጃ አብሮ ያልተያያዘ መሆኑ፤ xxv

❖ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ሚያዚያ፣ ግንቦት፣ ሰኔ፣ ሃምሌ፣ ነሃሴ /2015 ዓ.ም እና ታህሳስና የጥር /2016 የነዳጅ ቅባት እና ዘይት አጠቃቀም 4-24553፣ 426548፣ 4-03123፣ 4-27215፣ 4-23235፣4-23214፣ 4-24552፣ 4-24056፣ 4-26546፣ 4-17161፣ 4-04225 ተሽከርካሪዎች ለኃላፊዎች ተመድበው ነገር ግን አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የከተማና የመስክ ተሽከርካሪዎች መሆናቸው ቢገለፅም በመመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል 3 ተራ ቁጥር 2 መሰረት የነዳጅ ፍጆታቸው ከነምክንቱ /ከነመግለጫው ሪፖርት መደረግ የነበረበት ቢሆንም ያልተካተተ መሆኑን፤ xxv

❖ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የሃምሌ/2015 መስከረም፣ ጥቅምት፣ ህዳር፣ ታህሳስ፣ ጥሪ /2016 ዓ.ም የነዳጅ ቅባት እና ዘይት የነዳጅ ቅባት እና ዘይት አጠቃቀም ላ የተሞላ ዘይት፡- የታርጋ ቁጥር 32935 5,200 ሊትር፤ የታርጋ ቁጥር 23273፣ 8,400 ሊትር ሲሆን በዚህ መልኩ 9 ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፤ ታርጋ ቁጥር 35 ዕ/ድ 6394 ሊትር፣ 8,600 ሊትር፤ ታርጋ ቁጥር 4-30473 8,400 ሊትር፤ ታርጋ ቁጥር 4-18778 2,800 ሊትር በዚህ መልኩ 11 ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፤ታርጋ ቁጥር 4-30618- 6,200 ሊትር፣ ታርጋ ቁጥር 4-29757 - 6,200 ሊትር ሲሆን በዚህ መልኩ 11 ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፤ ታርጋ ቁጥር 4-18778- 8,145 ሊትር፣ 9 ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፤ በጥር/2016 ዓ.ም የታርጋ ቁጥር 4-34841 8,145 ሊትር፣ የታርጋ ቁጥር ዕድ-6394 8,145 ሊትር፣ ታርጋ ቁጥር 4-30618 8,145 ሊትር፤ ታርጋ ቁጥር 4-30473 6,030 ሊትር፣ የታርጋ ቁጥር 4-28924 8,145 ሊትር በዚህ መልኩ 12 ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፤ xxvi

አባሪ..7. የፌዴራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም የሚያገለግሉ ቅጾች ዝርዝር xxvi

አባሪ.8. የፍሊት ማናጅመንት በሙከራ ያሉ የፌደራል መ/ቤቶች ዝርዝር xxvii

የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ማጠቃለያ (Executive Summery)

የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በባለስልጣን መ/ቤቱ የተሽከርካሪ ስምሪት፣ አያያዝ እና የነዳጅ አጠቃቀም አፈፃፀም ውጤታማነትን በተመለከተ ስራውን ለማስፈጸም የወጡ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ስታንዳርዶች በተቀላጠፈና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና የተዘረጋው የአሰራር ሥርዓት ተፈፃሚ መደረጉን ማረጋገጥ ሲሆን በዚህ ጉዳይ ላይ የአሠራር ግድፈቶች ካሉ መንስኤያቸውን በመለየት የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብና ተጠያቂነትን ማስፈን ነው፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፍ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (International Standards of Superem Audit Institutions (ISSAI) እና በመንግስት መ/ቤቶች እና ድርጅቶች ላይ የክዋኔ ኦዲት ለማድረግ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በተሰጠው አዋጅ ቁጥር 982/2008 መሠረት ነው፡፡

ኦዲቱን ለማከናወን ከተቀመጠው የኦዲት አካባቢ ጋር ተያያዥ የሆኑ ማስረጃዎችን በመከለስና በመተንተን እንዲሁም ለሚመለከታቸው የባለስጣን መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች፣ በሰርቬይ እና በአካል በመሄድ በናሙና ለተመረጡ የፌደራል መ/ቤቶች ላሉ የስራ ሀላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ፣ በአካል ተገኝቶ ሰነዶቻቸው መከለስ እና የመስክ ምልከታ በማድረግ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

በኦዲቱ ወቅት የተገኙት ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

- በአዋጅ ቁጥር 1333/2016 ለማስፈጸም የሚያስችል አዲስ የግዥ መመሪያ ያልተዘጋጀ ወይንም ነባሩ መመሪያ ያልተሻሻለ መሆኑ፣
- የበላይ ኃላፊዎች፣ ከፍተኛ ኃላፊዎችና ኃላፊዎች በሚሰጣቸው/ በሚመደብላቸው ተሽከርካሪ የሚሰጥ ወርሃዊ የነዳጅና ጥገና ወጪያቸው ሪፖርት የሚደረግበት አሰራር ያልተቀመጠ መሆኑ፣
- ስለተሽከርካሪ አጠቃቀም የወጣ መመሪያ ከነማሻሻያው እንዲሁም በተለያየ ጊዜ ከጠቅላይ ሚኒስቴር እና ከገንዘብ ሚኒስቴር የሚተላለፉ መሰረት ተሽከርካሪዎችና ነዳጅ ስለመመደቡና ሥራ ላይ ስለመዋሉ ባለስልጣን መ/ቤቱ ያልተከታተለ እና ያልተቆጣጠረ መሆኑ፣ በሰርኩላሮች መሰረት ያልተገበሩ መ/ቤቶች መገኘታቸው፣





- ወርሃዊ የተሽከርካሪ ነዳጅ ቅባትና መለዋወጫ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ የማይልኩ ተቋማት መኖራቸው፣ ለሚልኩትም ተቋማት ባለስልጣኑ ገምግሞ ግብረ-መልስ እየሰጣቸው አለመሆኑ እና ሲልኩ የነበሩትም መላክ ያቆሙ መኖራቸው፤ የማይልኩትንም እየተከታተለ እንዲልኩ አለማድረጉ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ዓመታዊ የተሽከርካሪ መረጃዎች የማይልኩ ተቋማት መኖራቸው እና በማይልኩ ተቋማት ላይ ባለሥልጣኑ አስተዳዳራዊ እርምጃ እየወሰደ አለመሆኑ፤



- ባለስልጣን መ/ቤቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አገር አቀፍ የሥምሪት አስተዳደር (Fleet Management) ሶፈት ዌር በባህርዳር ዩንቨርስቲ አመካኝነት በጥቅምት 30/ 2015 የአንድ ዓመት ውል ተገብቶ እና ለምቶ ለሙከራ ሥራ 13 መ/ቤቶች የሙከራ ስራ ለመጀመር ሥልጠና ከመስጠት ባለፈ ወደ ተግበራ አለመግባቱ፣

- መ/ቤቶች ለ6፣ 7ና ከዛ በላይ ዓመታት ባስለኩት የነዳጅ ኖርማላይዜሽን ልኬት የሚጠቀሙም መኖራቸው፤
- በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ ነዳጅ አጠቃቀምና ጥገና መረጃ ልውውጥ የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ የተጠቀሱትን የኦዲት ግኝቶች ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ አዋጅ ቁጥር 1333/2016 ለማስፈጸም የሚያስችል የተዘጋጀው አዲስ የግዥ መመሪያ በማጸደቅ ወደ ተግባር ሊገባ፣ ለፌዴራል ተቋማትም ስለአፈጻጸሙ ሥልጠናና ግንዛቤ ማስጨበጥ የሚጠበቅበት እና ለአዋጁ አተገባበር የሚያስፈልግ ደንብ ካለም በማርቀቅ እንዲጸድቅ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡
- ❖ ሁሉም የፌዴራል ተቋማት ወርሃዊ የተሽከርካሪ ነዳጅ ቅባትና መለዋወጫ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ መላካቸውን ሊያረጋግጥ፣ የማይልኩትን ተቋማት እንዲልኩ ሊያደርግና በማይልኩትም ተቋማት ላይ ተጠያቂነትን የሚያሰፍን አሠራር በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በሙከራ ላይ ያለው የፍሊት ማኔጅመንት በተቻለ ፍጥነት ከሙከራ ደረጃ ወጥቶ በሁሉም የፌዴራል ተቋማት የሚተገበርበትን ስልት በመቀየስ ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በወረቀት ሆነ በሥርዓቱ የሚገኘውን መረጃ በመገምገም ለየተቋማት ግብረ መልስ መስጠትና በግብረ መልሱ መሰረት መፈጸሙን መከታተል ይጠበቅበታል፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ሁሉም ተቋማት የበላይ ኃላፊዎች፣ ከፍተኛ ኃላፊዎችና ኃላፊዎች በሚሰጣቸው /በሚመደብላቸው ተሽከርካሪ የሚሰጥ ወርሃዊ የነዳጅና ለጥገናቸው የሚወጣ ወጪ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ሪፖርት የሚያደረጉበት፣ የፍሊት ማኔጅመንት ሥርዓት ሲተገበርም መረጃውን ባለሥልጣኑ ተንትኖ ግብረ መልስ የሚሰጥበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል መንግስቱ በየአመቱ ለነዳጅ እና ለጥገና የወጣውን ወጪ አጠቃላይ ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት በሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ ለበላይ ኃላፊዎች፣ ለከፍተኛ ኃላፊዎች የሚመደቡ ተሽከርካሪዎች እና የተፈቀደ ነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ በሚኒስትሮች ም/ቤት፣ በጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት እና በገንዘብ ሚኒስቴር በወጡ መመሪያዎችና ሰርኩላሮች ተጠቃለው በሚዘጋጀው መመሪያ ውስጥ በማካተት ተግባራዊነታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም አዲሱ የፍሊት ማኔጅመንት

ሥርዓት ላይ ለበላይ ኃላፊዎች፣ ለከፍተኛ ኃላፊዎች የሚመደቡ ተሽከርካሪዎች እና የተፈቀደ ነዳጅ አጠቃቀም በአግባቡ ሊያካትት እና መረጃውንም መሰረት በማድረግ ትንተና ሊሠራና የፖሊሲ ኃሳብ ለሚመለከታቸው አካል በሪፖርት መልክ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አገር አቀፍ የሥምሪት አስተዳደር (Fleet Management) ለመዘርጋት ያስለማውን ሶፈት ዌር የሙከራ ትግበራውን በፍጥነት በማጠናቀቅና በሙከራ ትግበራ ወቅት የታዩ ክፍተቶችን በመሙላት በሁሉም የፌዴራል ተቋማት የሚተገበርበትና ስልት በመቀየስና ተገቢውን ሥልጠና በመስጠዋ በሁሉም ተቋማት ወጥ የሆነ አሠራር እንዲተገበር ሊያደርገ ይገባል፡፡ በፍሊት ማኔጅመንቱ ላይም በሁሉም የፌደራል መ/ቤቶች የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ለእያንዳንዳቸው የህይወት ታሪክ መዝገብ /ፋይል ማስገባት በየጊዜው ወቅታዊ ሊያደርጉና ባለስልጣን መ/ቤቱ ወቅታዊ መሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

Office of the Federal Auditor General

ክፍል አንድ

መግቢያ

የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን አመሠራረት

1. በአገራችን መንግስት ሥራ አገልግሎት የሚያስፈልጉ ገ1ዥዎች ሲፈጸሙ የነበረ ሲሆን ከ1935 ዓ.ም እስከ 1950 ዓ.ም የሁሉም መንግሥት መ/ቤቶች ግዥ ተጠቃሎ በገንዘብ ሚኒስቴር አማካኝነት ይከናወን እንደነበርና አፈፃፀሙ ከፍተኛ መዘግየትና አልፎ አልፎም የአገልግሎት መቋረጥ ይታይበት ስለነበር በገንዘብ ሚኒስቴር ይህ አሰራር ሙሉ ለሙሉ እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡ በየጊዜው የሚደረገውን ማሻሻያ ተከትሎ በ1997 ዓ.ም የመንግሥት ግዥን ሙሉ በሙሉ ለግዥ ፈፃሚ አካላት በመስጠትና ወደ አልተማከለ አሠራር እንዲቀየር ተደረጎ ለበርካታ አመታት ሲንከባለሉ ለቆዩት አብዛኞቹ የመንግሥት ግዥ አፈፃፀም ችግሮች መፍትሄ ለማምጣት፣ የግዥ መመሪያዎች፣ ደንብና የመንግሥት ግዥ አዋጅ ቁጥር 430/97ን በማሻሻል በአዋጅ ቁጥር 649/2001 ዓ.ም ተጠሪነቱ ለቀድሞ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር (በአሁኑ ገንዘብ ሚ/ር) የሆነ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ተቋቋሞ የመንግሥት ግዥ አፈፃፀምንና የንብረት አስተዳደሩን እየመራ ይገኛል፡፡ ኤጀንሲው የተቆጣጣሪነትን የሚሰራ በመሆኑ በፌደራል አስፈጻሚ አካላት በ2014 ዓ.ም አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት የመንግስት ግዥ እና ንብረት ባለስልጣን በመባል እንደገና ተደራጅቷል፡፡

የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ራዕይ፣ ተልዕኮ፡

ራዕይ (Vission)

2. **በ2017 ዓ.ም በአፍሪካ ተፎካካሪ የመንግስት የግዥና ንብረት ተቆጣጣሪ ተቋም ሆኖ መገኘት፤**

ተልዕኮ (Mission)

3. የመንግስት ግዥና ንብረት ሥርዓትና ቁጥጥርን በማጠናከር ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ከፍተኛ ጥቅም እንዲያስገኝ ማስቻል፤

ዓላማ (Objective)

4. የባለሥልጣኑ ዓላማ አስፈላጊውን አቅም በመገንባት፣ የመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አስተዳደር የዚህን አዋጅና በአዋጁ መሰረት የወጡትን መመሪያዎች የጠበቀ መሆኑን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ማረጋገጥ እንዲሁም የግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓቱን ለማሻሻል ለሚቀርብ ሀሳብ መሰረት የሚሆኑ የጥናት ሥራዎችን በማከናወን ዘላቂ የሆነ፣ ውጤታማ ቀልጣፋ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደርን ማሳካት ነው፡፡

የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ስልጣንና ተግባር

5. የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 1333/2016 ዓ.ም መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡

- ❖ በመንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር ፖሊሲዎች፣ መርሆዎችና አፈፃፃም ላይ የፌደራል መንግስትን ማማከር፣ ክልሎች እና ለከተማ መስተዳደሮች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፤
- ❖ በመንግስት ግዥ አፈጻጸምና ንብረት አስተዳደር ሥርዓትና አተገባበር ላይ ጥናት ማከናወን እንዲሁም በጥናቱ ላይ ተመስርቶ ሥርዓቱን ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፤
- ❖ ከመንግስት መ/ቤቶች የሚቀርብት መረጃ መሰረት በማድረግ የመንግስት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ስርዓት አፈፃፀም በሚመለከት የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፣ ሚኒስቴሩ በሚጠይቀው ዝርዝር መሠረት በእያንዳንዱ መንግሥት መሥሪያ ቤት ስለተከናወነው ግዥ ዓይነት እና መጠን እንዲሁም ንብረት አስተዳደር ጉዳዮች መረጃዎችን መስጠት፤
- ❖ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 87 ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተዘረዘሩትን ኃላፊነትን ባለመወጣት የሚያስጠይቁ ጥፋቶች የፈፀመ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተሿሚ ወይም የተመደበ ሰው ላይ አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲወሰን ለሚኒስትሩ ሪፖርት ማቅረብ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General

- ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር የመንግስት መ/ቤቶች ለሚፈለጉ ተመሳሳይ ንብረቶች ደረጃ ማውጣትና የወጡ ደረጃዎች ወጥነት ባለው መንገድ ስራ ላይ እንዲዉሉ ማድረግ፤

- የግዥና ንብረት አስተዳደር የሕግ ማዕቀፍን ስራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ የሆኑ መደበኛ የጨረታ ሰነዶችን ማዘጋጀት ማጽደቅ፣ የግዥ ዝርዝርና ካታሎግ ልዩ ልዩ ቅፃችን፣ ማኑዋሎች እንዲሁም የግዥና ንብረት ሙያተኞች እና ኃላፊዎች ሊከተሏቸው የሚገባ የሥነ ምግባር መርሆዎችን ማዘጋጀት እና ሥራ ላይ እንዲውለ ማድረግ፤

- በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት የተዘጋጁ መረጃዎች፣ እንዲሁም በግዥ አፈፃፀም እና በንብረት አወጋገድ ሂደት ጥፋት በመፈጸማቸው ለባለሥልጣኑ በቀረቡ የጥፋተኝነት ሪፖርቶች ላይ የተሰጡ ውሣኔዎች፣ የኦዲት ውጤቶች እና ሌሎች ሕዝብ ሊያውቃቸው የሚገቡ ዋና ዋና ጉዳዮችን በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሰረት እና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለሕዝብ ይፋ ማድረግ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General

- ከሚኒስቴሩ እና ሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መሥሪያ ቤቶች ካላቸው የሥራ ባህሪ በመነሳት ሊኖራቸው የሚገባውን የግዥና ንብረት አስተዳደር እና ተያያዥ ስራዎች አደረጃጀት አጥንቶ ማቅረብ፣ ተፈጻሚነቱን መከታተል፤

- በመንግስት ግዥ ወይም በሚወገድ ንብረት ሽያጭ ጨረታ ለመሳተፍ ፍላጐት ያላቸው ተወዳዳሪዎች የሚመዘገቡበትን ዘመናዊ ሥርዓት መዘርጋትና ማስተዳደር፤

- የተቋም እና የሰው ኃይል አቅም ለማጐልበት የሚያስችል የአቅም ግንባታ እስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት እና የአቅም ግንባታ ሥልጠና መስጠት፤

- ለመንግሥትግዥ አፈጻጸም እና ንብረት አስተዳደር የሚያገለግል የመረጃ ቋት ማቋቋም፣ ማጐልበት፣ መጠበቅ እና ወቅታዊነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፤

- በፌዴራል እና በክልል መንግስታት መካካል የተጣጣመ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት እንዲኖር ዕገዛ ማድረግ፤

- የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር፣ እንዲሁም የመንግሥት እና የግል አጋርነት ዘርፍ ግዥዎችን አፈፃፀም በራሱ ዕቅድ፣ እንዲሁም ጥፋት ስለመፈፀሙ ጥቆማ ሲቀርብለት ሂደቱን በማስቆም የሥርዓት መጠበቅ ወይም የክዋኔ ኦዲትና ክትትል የማካሄድ እና በግኝቱ መሰረት ተገቢውን እርምጃ እንደአግባብነቱ በራሱ መውሰድ ወይም ስልጣን ባላቸው ሌሎች አካላት እንዲወሰድ ማድረግ፤
- የሚቀርቡ የጥፋተኝነት ሪፖርቶችን በማጣራት ጥፋት የተፈፀመ መሆኑን ሲያረጋግጥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 84 መሰረት እንደጥፋቱ ክብደት ማስጠንቀቂያ የመስጠት፣ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ በመንግሥት ግዥ ወይም የመንግስትን ንብረት በሽያጭ ለማስወገድ በሚወጣ ጨረታ እንዳይሳተፉ ማገድ፤
- የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ተግባራት ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚወጡ መመሪያዎችን ተከትሎ መፈጸማቸውን መከታተልና መቆጣጠር፣ እንዲሁም ከመሥሪያ ቤቶች፣ ከአቅራቢዎች ወይም ከህዝብ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መሰረት በማድረግ ምርመራ ማድረግና እርምት እንዲወሰድ ማድረግ፣ እንደሁኔታው አስተዳደራዊ እርምጃ የመውሰድ ስልጣን ላለው አካል ማሳወቅ፤
- በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (15) ዓላማ፣ እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት ሰነዶች፣ መዛግብት፣ ሪፖርቶች እና ማናቸውም ሌሎች ማስረጃዎች ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ከተወዳዳሪዎች፣ ከተጫራቾች ወይም ከአቅራቢዎች እና ከሌላ ማንኛውም ሰው እንዲቀርቡለት የማዘዝ፣ እንዲሁም ምስክሮችን በመጥራት፣ ምስክሮችና ግዥው ወይም የሚወገደው ንብረት ሽያጭ የሚመለከታቸው ወገኖች ቃላቸውን በመሐላ እንዲሰጡ ማድረግ፤
- በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (15) መሰረት በሚያደረገው ቁጥጥርና ምርመራ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ወይም ወንጀል እንዲታይ ማድረግ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ለሚመለከተው የሕግ አካል ማሳወቅ፣
- እንደአስፈላጊነቱ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ሙያተኞች ሊኖራቸው የሚገባውን ዕውቀትና ክህሎት መወሰን፣ የሙያ ብቃት የማረጋገጫ ምስክር

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

ወረቀት መስጠት፣ ሙያተኞችን መመዝገብና መቆጣጠር፣ የግዥና ንብረት አስተዳደር ሙያተኞች ማህበር እንዲቋቋም ድጋፍ ማድረግ፣ እንዲሁም የሚቋቋመው የሙያተኞች ማህበር በሕግ የሚሰጠውን ኃላፊነት መወጣት በሚችልበት አቋም ላይ ሲደርስ እንደሁኔታው ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት

እንዲያከናውን ውክልና መስጠት፤

- ❖ አግባብነት ባለው የክልል መንግሥት አካል በክልሉ የመንግሥት ግዥ እና ሚወገድ ንብረት ሽያጭ ላይ እንዳይሳተፍ ተጫራች ወይም አቅራቢ በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ግዥ እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ላይ እንዳይሳተፍ ማገድ፤

- ❖ ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሙያ ዕድገት ከሚሰሩ እና በዘርፉ ለመሳተፍ ፍላጐት ካላቸው አካላት ጋር ተቋማዊ ግንኙነት በመፍጠር ተባብሮ መስራት፤

- ❖ በፌዴራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሥር ያልሆነን የፌዴራል መንግስት ንብረት ወይም በሕግ ወይም ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ የፌደራል መንግስት ንብረት እንዲሆን የተደረገ ማናቸውንም ንብረት በመንግስት ንብረትነት የመያዝ፣ የማስተዳደር፣ በሚኒስትሩ ውሳኔ መሰረት እንዲወገድ የማድረግ፤

- ❖ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በጤና ወይም በአከባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ጊዜያቸው ያለፈባቸው አደገኛ ኬሚካሎች ወይም የኬሚካል ውጤቶች፣ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ የኤሌክትሮኒክ ዕቃዎች፣ መድኃኒቶች፣ ጨረራ አመንጪ ዕቃዎች፣ የኢንዱስትሪ ዝቃጮችና የግብርና ተረፈ ምርቶች አያያዝና አጠባበቅ፣ እንዲሁም አወጋገድ ላይ ጥናት በማከናወን የአሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ፤

- ❖ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚኒስትሩ የሚዘረጋውን ዘመናዊ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር የኤሌክትሮኒክ አሰራር ሥርዓት መቆጣጠር፣ ማስተዳደር፤

- ❖ በዚህ አዋጅ ሌሎች አንቀጾችና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች ለባለስልጣኑ

የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት መወጣት፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

የባለስልጣን መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል አደረጃጀት

ድርጅታዊ መዋቅር

6. የባለስልጣን መ/ቤቱ በአንድ ዋና ዳይሬክቶር የሚመራና ተጠሪነቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሲሆን አንድ ምክትል ዋና ዳይሬክቶር፣ አንድ የዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት እና አንድ የሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈጻሚ በስሩ አሉት፡፡ ባለስልጣኑ ተጠሪነቱም ለገንዘብ ሚኒስቴር ነው፡፡ በሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈጻሚ ስር ስድስት (6) ስራ አስፈጻሚ፤ በዋና ዳይሬክቶር ጽ/ቤት ስር አምስት (5) ስራ አስፈጻሚ፤ በምክትል ዋና ዳይሬክቶር ስር ሶስት (3) ስራ አስፈጻሚ እና ዘጠኝ (9) ዴስኮች እንዲሁም በኦዲት ስራው በዋናነት የሚመለከተው የስራ ክፍል የመንግስት ግዥ እና ንብረት ማሻሻያና አቅም ግንባታ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ሶስት ዴስኮች ተደርገው ተዋቅሯል፡፡ የድርጅታዊ መዋቅሩ ዝርዝር በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡

የሰው ኃይል

7. ባለስልጣኑ መ/ቤቱ የሰው ኃይል በተመለከተ፡ ከ2014 እስከ 2016 ዓመት በጀት የተፈቀደለት የሰው ኃይል ለመደበኛ 628፤ ለፕሮጀክት 176 በአጠቃላይ 804 የሰው ኃይል ነው፡፡ ለመደበኛ በመዋቅሩ ከተፈቀደለት የሰው ኃይል የተሟላ መደብ 351 (55%)፣ ክፍት የስራ መደብ 277 (45%) ነው፡፡ በ2017 ሁለተኛ ሩብ በጀት ዓመት ለመደበኛ የተፈቀደው የሰው ኃይል 202 ሲሆን የሰው ኃይል የተሟላ መደብ 104 (51%)፣ ክፍት የስራ መደብ 98(48%) ነው፡፡ እንዲሁም የመንግስት ግዥ እና ንብረት ማሻሻያና አቅም ግንባታ መሪ ሥራ አስፈጻሚ የሚያስፈልገው የሰው ኃይል 29 ሲሆን የተሟላው መደብ 15 (51 በመቶ) ያልተሟላ 14 (49 በመቶ) መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የባለስልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

8. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት እና በዕቅድ የያዛቸውን ሥራዎች ለማስፈፀም የሚያስፈልገውን ገቢ የሚያገኘው መንግሥት በሚመድብለት መደበኛ በጀት እና በራሱ ፕሮጀክቶች ሲሆን፣ ከ2014 እስከ 2017 ሁለተኛ ሩብ

ዓመት ላከናወናቸው ተግባራት የተመደበና ወጪ የሆነ የመደበኛ እና የፕሮጀክት በጀት ዝርዝር ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ተመላክቷል፡፡

የመደበኛ በጀት፡

በጀት አመት	የተመደበ መደበኛ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ	ሥራ ላይ ያልዋለ መደበኛ በጀት	አፈፃፀም በመቶኛ
2014	53,730,421.04	52,339,311.82	1,391,109.22	97.4%
2015	23,986,900.00	23,541,910.73	444,990.00	98%
2016	25,350,000.27	16,334,813.88	9,015,186.39	64.44%
2017 እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2017	29 000 000.00	17 176 058.03	11,823,941.97	40.77

በጀት አመት	የተመደበ የፕሮጀክት በጀት	ሥራ ላይ የዋለ	ሥራ ላይ ያልዋለ መደበኛ በጀት	አፈፃፀም በመቶኛ
2014	70,666,759.4	59 759 935.75	10,906,823.65	**85**%
2015	200,927,905.55	168 596 640.63	32,331,264.92	84%
2016	158,610, 393.75	150 257 750.93	8,352,642.82	**95**%
2017 እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2017	53 613 716.93	23 160 808.98	30,452,907.95	**68**%

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

ኦዲቱ አላማ

9. የክዋኔ ኦዲቱ አላማ በባለስልጣን መ/ቤቱ የተሽከርካሪ አያያዝና ስምሪት እንዲሁም የነዳጅ አጠቃቀም አፈፃፀም ውጤታማነትን በተመለከተ ስራውን ለማስፈጸም የወጡ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ስታንዳርዶች፣ በተቀላጠፈና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና የተዘረጋው የአሰራር ሥርዓት ተፈፃሚ መደረጉን ማረጋገጥ ሲሆን በዚህ ጉዳይ ላይ የአሠራር ግድፈቶች ካሉ መንስኤያቸውን በመለየት የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብና ተጠያቂነትን ማስፈን ነው፡፡

ኦዲቱ አካባቢ (Audit Area)

10. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ "የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪ ስምሪት፣ አያያዝ እና የነዳጅ አጠቃቀም አፈፃፀምን ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

11. ከላይ የተጠቀሰውን የኦዲት አካባቢ ለመገምገም እና የዝርዝር ኦዲት ለማከናወን ሦስት ዋና ዋና የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝ እና የነዳጅ አጠቃቀምን ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ ለማድረግ፣ ለመቆጣጠር ለመከታተል የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ዘርጎቶ ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፡፡
2. ባለስልጣን መ/ቤቱ የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝ እና የነዳጅ አጠቃቀምን ውጤታማ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር እና የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria)

12. በኦዲት ቡድኑ የተመረጡ ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ ሃያ (20) የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criterias) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፍርቱን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት ባለስልጣኑ የተቋቋመበት አዋጅ ቁጥር 649/2001፣ የተሽከርካሪና የነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ 32/2004፣ የህጋዊነት የኦዲት ማኑዋል፣ ስለተሽከርካሪና ነዳጅ አጠቃቀም በ2011 እና 2012 በጠቅላይ ሚኒስቴሩ ጽ/ቤት በሚኒስትሮች ም/ቤት፣ በ2009 በሚኒስትሮች ም/ቤት እና በገንዘብ ሚ/ር የወጡ ሰርኩላሮች፣ ከ2014 እስከ 2016 ዓመታዊ እና ስትራቴጂክ እቅዶች፣ በ2014 ዓ.ም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተጠና ጥናት፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

የመንግስት ግዥ እና ንብረት ማሻሻያና አቅም ግንባታ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ስራ መዘርዝር/ ተግባርና ኃላፊነት ናቸው፡፡ ባለስልጣን መ/ቤቱ ከኦዲት ቡድኑ ጋር የተስማሙበት መመዘኛ መስፈርቱ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዞዋል።

የኦዲት ወሰንና ዘዴ

የኦዲቱ ወሰን

13. የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፍ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (International Standards of Supreme Audit Institutions (ISSAI) እና በመንግስት መ/ቤቶች እና ድርጅቶች ላይ የክዋኔ ኦዲት ለማድረግ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በተሰጠው አዋጅ ቁጥር 982/2008 መሠረት ነው፡፡

14. ኦዲቱ የሸፈነው ጊዜ ከ2014 በጀት ዓመት እስከ 2017 ሁለተኛ ሩብ አመት ድረስ ያለውን ጊዜ ሲሆን የተሽከርካሪ ስምሪት፣ አያያዝ እና የነዳጅ አጠቃቀም አፈፃፀም ውጤታማነትን ጋር በተያያዘ የተከናወኑ ሥራዎች ላይ ነው፡፡ ኦዲቱ የተከናወነው በዋናነት በመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን መ/ቤት ሲሆን በተሽከርካሪና ነዳጅን ባለስልጣኑ የሚቆጣጠራቸው የፌደራል መ/ቤቶች፡ 18 በአዲስ አበባ በአካል በመሄድ እና 30/ 70በመቶ/ የሚሆኑ የኒቨርሲቲዎች እና 3 የፌደራል መ/ቤቶች መጠይቁ እና ቼክ-ሊስት በመላክ (Survey) ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡ (በመስክ የታዩት ዝርዝር **በአባሪ 4 እና 5 ተያይዟል**)፡፡

የኦዲቱ ዘዴ

15. ኦዲቱን ለማከናወን ከተቀመጠው የኦዲት አካባቢ ጋር ተያያዥ የሆኑ ማስረጃዎችን በመከለስና በመተንተን እንዲሁም ለሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች፣ በናሙና ተመረጡ በአካል እና በሰርቨይ በታዩ የፌደራል መ/ቤቶች የስራ ሀላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ፣ የተሽከርካሪ እና የነዳጅ ሰነዶቻቸውን በመከለስ እንዲሁም የመስክ ምልከታ በማድረግ ኦዲቱ ተከናውኗል፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር Office of the Federal Auditor General

የአሰራር ስርዓት መግለጫ

/Process description/

16. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች በንብረት አስተዳደር (ተሽከርካሪና ነዳጅ) አጠቃቀማቸውን ለመከታተል የመንግስት ግዥ እና ንብረት ማሻሻያና አቅም ግንባታ መሪ ሥራ አስፈጻሚ የአሰራር ስእላዊ መግለጫ ያላቀረቡ ሲሆን የህጋዊነት ኦዲት መሪ ስራ አስፈፃሚ እንድንጠቀም ይህንን ሰጥቶናል፤ ኦዲት ለማድረግ በመደበኛ እና በጥቆማ የሚከናወኑ የኦዲት ስራዎች ዓመታዊ እቅዶች በማዘጋጀት ከታች በስእላዊ መግለጫው የተጠቀሱት ስራዎች ቀጥሎ ተመልክተዋል፡፡



ክፍል ሁለት

ግኝቶች

የተሽከርካሪ አያያዝ፣ ስምሪት እና የነዳጅ አጠቃቀም የአሰራር ሥርዓት ተግባራዊ እና ወቅታዊ መደረጉን በተመለከተ

17. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎች አመዘጋገብ፣ አያያዝ፣ ስምሪት፣ ቁጥጥር እና የነዳጅ አጠቃቀም ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ የአሰራር ሥርዓት በየጊዜው ወቅታዊ እያደረገ ሊዘረጋ፤ በሚወጡ የህግ ማእቀፎች እና አፈፃፀም ላይ ሀሳብ ሊሰጥ ይገባል::

18. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ❖ መመሪያ ቁጥር 32/2004 ማስፈፀሚያ መመሪያ ለ16 ዓመታት የቆየ መሆኑ፤ ወቅታዊ ያልተደረገ አለመደረጉ፣
- ❖ አዋጁ ቁጥር 649/2001 በአዋጅ በቁጥር 1333/2016 ጳጉሜ 4 ቀን 2016 የተሻሻለ ቢሆንም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአስራርና የሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 አንቀጽ 60/6 ላይ አዋጁ በወጣ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ መመሪያ መውጣት እንዳለበት በተደነገገው መሰረት አዲስ መመሪያ ያልተዘጋጀ ወይንም ነባሩ መመሪያ ያልተሻሻለ መሆኑ፣
- ❖ በናሙና ተመርጠው የታዩ የፌደራል መ/ቤቶች የተሻሻለው የመንግስት ግዥና ንብረት አዋጅ ቁጥር 1333/2016 ወደ ትግበራ ያልተገባ መሆኑ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ የገለፁ መሆነ፤
- ❖ የበላይ ኃላፊዎች፣ ከፍተኛ ኃላፊዎችና ኃላፊዎች በሚሰጣቸው/በሚመደብላቸው ተሽከርካሪ የሚሰጥ ወርሃዊ የነዳጅና ጥገና ወጪያቸው ሪፖርት የሚደረግበት አሰራር አለመኖሩ መሆኑ፣
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና መመሪያው ቁጥር 32/2004 ተግባራዊነቱን አለመከታተሉ ወጥነት ያለው አሰራር አለማድረጉ ለአብነት፡ የመ/ቤቶች የመካከለኛ ኃላፊዎች ነዳጅና ተሽከርካሪ አመዳደባቸው፣ የነዳጅ አጠቃቀም ላይ ወጥነት የሌለው /የተለያየ አሰራር የሚጠቀሙ መሆኑ፤
- ❖ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ የፌዴራል መ/ቤቶች ውስጥ መመሪያ ቁጥር

32/2004 እና የነዳጅ ሰርኩላር አሰራሩን ከጠቅላይ ሚ/ር ጽሕፈት ቤት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሚኒስትሮች ም/ቤት በነሃሴ 16/2011 እና በሕዳር 18/2012 ዓ.ም በቁጥር መ30-899/56 የተላለፈ፣ በ2009 ዓ.ም ስለተሽከርካሪ አጠቃቀም የወጣ መመሪያ እና በገንዘብ ሚ/ር በ2009 ዓ.ም የተላለፉ ሰርኩላሮች **ያልተገበሩ** መ/ቤቶች ያሉ መሆኑ (ለአብነት፡- ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እስከ ጥር 2016 ዓ.ም እንዲሁም ኦዲቱ እስከ ተከናወነ ድረስ ቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል፣)

- በናሙና ተመርጠው የታዩ የፌደራል መ/ቤቶች ብዙዎቹ ለበላይ ኃላፊዎች እና ከፍተኛ ኃላፊዎች የሚመደቡ ተሽከርካሪዎች ብዛት፣ በዓይነትም ነዳጅ ቆጣቢ ተሽከርካሪዎች እንዲሆኑ ከገንዘብ ሚ/ር በቁጥር በተ8/6/159 በቀን 2/2/2014 በተላለፈ ሰርኩላር እና ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በቁጥር መ30/8997 በቀን ህዳር 18/2012 ዓ.ም በተላለፈ ሰርኩላር ለዋና ዳይሬክተሮችና ለምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ አንድ ተሽከርካሪ ከሚመደብ በስተቀር ለቤተሰቦቻቸው የሚመደብ ተሽከርካሪ አለመኖሩን የገለፀ ቢሆንም ይህንን እየተገበሩት አለመሆኑ (ለማሳያ፡ ገንዘብ ሚ/ር፣ ገቢዎች ሚ/ር፣ መዐድን ሚ/ር፣ ፌደሬሽን ም/ቤት፣ መቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲና ሰመራ ዩኒቨርሲቲ፣ የግዥና ንብረት ባለስልጣን፣ ግብርና ምርምር፣)
- በተሽከርካሪ እና ነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ 32/2004 አባሪ የተደረጉ 13 ቅጾቹም ወቅታዊ ያልተደረጉ፤ በናሙና የታዩ መ/ቤቶች አብዛኛው ቅፆች እየተጠቀሚቸው አለመሆኑ፤ (**13 ቅፆች ዝርዝር በአባሪ 6 ይመልከቱ**)

  ለአብነት፡- የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ በ2013 ዓ.ም ቅፅ 5፣ 10፣ 11፣ 13ን ያልተገበራቸው መሆኑን እና በታህሳስ 2017 ደግሞ ቅፅ የመንግሰት ተሽከርካሪዎች ዕለታዊ የነዳጅ፣ የዘይትና የኪ.ሜ መመዝገቢያ ቅጽ 2፣ የመንግስት ተሽከርካሪ ወርኃዊ የነዳጅ፣ የዘይትና ጥገና ወጪ ማጠቃለያ ቅጽ 3፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች የህይወት ታሪክ መመዝገቢያ ቅጽ 4፣ ልዩ መታወቂያ 7፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች የነዳጅ፣ የዘይትና የቅባት መጠየቂያ ቅጽ8፣ የተሽከርካሪዎች የአደጋ መግለጫ ቅጽ 13፣ ያልተገበረ መሆኑ ፡
- የፌደራል መ/ቤቶች በሰርኩላሮቹ እንደ የተቋማቸው ዓይነት የበላይ ኃላፊዎች ተብሎ የተገለፁ የሚመደቡ ተሽከርካሪዎች ብዛት፣ በዓይነትም ነዳጅ ቆጣቢ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

ተሽከርካሪዎች (አውቶሞቢሎች) እንዲጠቀሙ እና ስለነዳጅ አጠቃቀም ከጠቅላይ ሚ/ር ጽሕፈት ቤት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሚኒስትሮች ም/ቤት በነሃሴ 16/2011 እና በሕዳር 18/2012 ዓ.ም በቁጥር መ30-899 የተላለፈ ሰርኩላር እንዲሁም በ2009 ዓ.ም በሚኒስትሮች ም/ቤት በተሽከርካሪ አጠቃቀም የወጣ መመሪያ እና በገንዘብ ሚ/ር በ2009 ዓ.ም የተላለፍ ሰርኩላሮች እየተገበሩዋቸው ባለመሆኑ የኦዲት ግኝት ተደርጎ እርምጃ ባለመወሰዱና የሚመለከተው አካል እርምጃ እንዲወስድ አለመደረጉ፤

- ❖ በሰርኩላሮቹ መሰረት እንደየተቋማቸው ዓይነት የበላይ ኃላፊዎች ተብሎ ለተገለፁት የሚመደቡ ተሽከርካሪዎች ብዛት እንደየ ኃፊነታቸው 2 እና 1፣ በዓይነትም ነዳጅ ቆጣቢ ተሽከርካሪዎች (አውቶሞቢሎች) እየተጠቀሙ ስለመሆናቸውና አለመሆናቸው እና ስለነዳጅ አጠቃቀም ክትትል መደረጉን የሚያሳይ ሪፖርት ተጠይቆ ለኦዲት አለመቅረቡ፤

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች፣ በናሙና ተመርጠው በታዩ የፌደራል መ/ቤቶች እና ለባለስልጣኑ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ -መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

19. ለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅ፣ ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ፡-

- ከላይ የተገለፁ ሃሳቦች ትክክል መሆናቸው፤ እየተከታተሉና እየተቆጣጠሩ አለመሆኑ፤ ሽፋኑና ጥራቱ አናሳ ቢሆንም ህጋዊነት ኦዲት ሲሰራ ስለተሽርካሪ የሚያዩበት ሁኔታ ሊኖር ቢችልም የሚወሰድ እርምጃ ስለማይኖር ውጤት እንዳላመጣ፤
- አዋጅ ቁጥር 1333/2016 ጳጉሜ 4 /2016 ታትሞ ሥራ ላይ የዋለ ቢሆንም፤ የአፈፃፀም መመሪያ በ3 ወር ጊዜ ዉስጥ መዘጋጀት ቢኖርበትም በበፊቱ አዋጅና መመሪያ ላይ ያልነበረ የልማት ድርጅቶችን የሚመለከቱ አንቀጾች በአዋጅ እንዲካተቱ በመደረጉ የሚዘጋጁ መመሪያዎችን ከዚህ አንጻር ማጣጣም በማስፈለጉ እና ከዚህ በፊት በተለያዩ መመሪያዎችና ሰርኩላሮች አማካኝነት የተላለፉ ሥርዓቶችን በሙሉ በአንድ መመሪያ ውስጥ እንዲካተቱ አስፈላጊ በመሆኑ እንዲሁም የመመሪያው ይዘት ከፍ ያለ እና ጊዜውን

የሚዋጁ አዳዲስ የግዥ ሥልቶች፣ የኤሌክትሮኒክ የግዥና ንብረት ሥርዓት እንዲሁም ዘለቄታዊ የግዥ አፈጻጸምና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት /Sustainable procurement/ እንዲያካትት በማስፈለጉ የዘገየ መሆኑና አሁን ረቂቅ መመሪያው ተጠናቆና ግብአት ከተሰበሰበ በኋላ ለአስተያየት ወደ ፍትህ ሚኒስቴር በየካቲት 11/2017 ዓ.ም መላኩንና

- በግኝትነት የተጠቀሱ ክፍተቶችም ሁሉም መመሪያዎችና ሰርኩላሮች በአዲሱ መመሪያ እንዲካተት በመደረጋቸው እንዲሁም በሙከራ ትግበራ ላይ ያለው የፍሊት ማኔጅመንት ሥርዓት ተግባራዊ ሲሆን እና አዲሱ መመሪያው ሲፀድቅና ሲተገበር የሚፈቱ መሆኑን፣

ገልጸዋል፡፡

20. የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎች አመዘጋገብ፣ አያያዝ፣ ስምሪት፣ ቁጥጥር እና የነዳጅ አጠቃቀም ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ የአሰራር ሥርዓት አለመዘርጋቱ እንደ ምክንያት ተወስደዋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

21. በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎች አመዘጋገብ፣ አያያዝ፣ ስምሪት፣ ቁጥጥር እና የነዳጅ አጠቃቀም ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ የአሰራር ሥርዓት በየጊዜው ወቅታዊ እያደረገ ካልዘረጋ እና ተግባራዊነቱን ካልተከታተለ ከወቅቱ ጋር መራመድ እንዳይቻል፣ የተዘረጉ አሰራሮች እንዳይተገበሩና ወጥነት ያለው አሰራር እንደይኖር ያደርጋል፡፡

ለበላይ ኃላፊዎች በህግ በተፈቀደው መሰረት ተሽከርካሪዎች ስለመመደቡንና ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጡን በተመለከተ፡-

22. ባለስልጣን መ/ቤቱ በፌዴራል መ/ቤቶች ለበላይ ኃላፊዎች፣ ለከፍተኛ ኃላፊዎችና ኃላፊዎች በህግ በተፈቀደው መሰረት መመደቡትን ሥራ ላይ መዋሉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

23. በየተቋማቱ ለበላይ ኃላፊዎች፣ ለከፍተኛ ኃላፊዎች እና ለኃላፊዎች የሚመደቡትን ተሽከርካሪዎች በተመለከተ
    - አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና አሁን የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1333/2016
    - የከፍተኛ ኃላፊችን ደመወዝና ጥቅማጥቅሞችን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት መመሪያ 32/2004 ጥቅምት 19 ቀን 1997 የወጣ እና ነሐሴ 4 ቀን

2011 እንደተሻሻለ፣

- የፌዴራል መንግስት ኃላፊዎች እና የሌሎች ተቋማት ተሽከርካሪዎች አጠቃቀምን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት መመሪያ ሐምሌ 28 ቀን 2009፣
- ህዳር 18 ቀን 2012 ዓ.ም. የተሽከርካሪ አጠቃቀምን በተመለከተ ጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት የተላለፈ ሰርኩላር፣
- የፌዴራል ተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ሰኔ 15 ቀን 2004 ዓ.ም. በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የወጣ፣ እንዲሁም
- የገንዘብ ሚኒስቴር ሐምሌ 2009 ያስተላለፈው ሰርኩላር፣

ወጥተዋል፡፡

24. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት

❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ ለበላይ ኃላፊዎች፣ ለከፍተኛ ኃላፊዎች በህግ (በጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት በሚኒስትሪዎች ም/ቤት ነሃሴ በ2011 እና በህዳር 2012 እና 2009 ዓ.ም የተላለፉ ሚኒስትሮች) በተፈቀደው መሰረት ስለመመደቡና ሥራ ላይ ስለመዋሉ ያልተከታተለ እና ያልተቆጣጠረ መሆኑ፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

ለማሳያ፡-

- በሚኒስትሮች ም/ቤት በቁጥር ምም 30 — 15/170 በቀን 24 ነሃሴ 2009 ዓ.ም የተላለፈ ሰርኩላር የፌደራል መ/ቤቶች ከፍተኛ ኃላፊዎች ወጪ ቆጣቢ፣ ውጤታማ እና ቀጣይነት ያለው ሰርቪስ እና ስታንዳርድ ያለው በሃገር ውስጥ በማምረት /ምርት በማእከል ግዥ ተከናውኖው ፍትሃዊ የሆነ አውቶሞቢል ተሽከርካሪ እንዲመደብላቸው፤ ነገር ግን ቪ8፣ ጂ9፣ ፕራዶ፣ ፓጃሮ፣ ወዘተ. በፑል አገልግሎት ለመስክ ስራ ብቻ እንዲውሉ ይህም እንደስራቸው ባህሪ ከ1 እስከ 3 እንዲመደብላቸው እና በውጭ ሃገር በብድር ወይም በእርዳታ ለፕሮጀክት የተገዙ ስቴሽን ዋገኖችን ለከተማ አገልግሎት መጠቀም እንደሌለባቸው የተቀመጠ ቢሆንም ከፍተኛ ኃላፊዎች ግን የሚጠቀሟቸው ተሽከርካሪዎች ቪ8፣ ጂ9፣ ፕራዶ፣ ፓጃሮ፣ ወዘተ. መሆኑ፤
- ሚያዝያ 2011 ዓ.ም ከገንዘብ ሚ/ር ለተጠሪው ባለስልጣን መ/ቤቱ የተላለፈው ሰርኩላር ለከፍተኛ ሃላፊዎች ለቤተሰብ ለተመደበ መኪና በወር 200 ሊትር

ቢመደብም ተደጋጋሚ ቀናት ለፑል ከተመደቡ ተሽከርካሪዎች ለቤተሰብ የሚጠቀሙ መ/ቤቶች መኖራቸው (ለማሳያ ኢንዱስትሪ ሚ/ር)

- ከጠቅላይ ሚ/ር ጽሕፈት ቤት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሚኒስትሮች ም/ቤት በነሃሴ 16/2011 እና በቁጥር መ30-899/56 በተላለፍ ሰርኩላር ለከፍተኛ ሃላፊዎች ለቤተሰብ ለተመደበ መኪና በወር 200 ሊትር ቢመደብም ተደጋጋሚ ቀናት ለፑል ከተመደቡ ተሽከርካሪዎች ለቤተሰብ የሚጠቀሙ መ/ቤቶች መኖራቸው (ለማሳያ ኢንዱስትሪ ሚ/ር)
- ፍትህ ሚኒስቴር ለበላይ ሃላፊዎች ለያንዳንዳቸው የተመደላቸው የተሽከርካሪ ብዛት እንዳለ ሆኖ ነገር ግን በጽ/ቤት ኃላፊ በሚል ብቻ በግልፅ ያልተቀመጡ 7 ተሽከርካሪ እና 5 ተሽከርካሪዎች የተኞች የበላይ ኃላፊዎች መሆናቸው ባልተገለፁ የተመደቡ መሆኑ፤

❖ በኦዲት ስራው በናሙና ከታዩ መ/ቤቶች ሚኒስትሮች እና የሚኒስትር ዴኤታዎች በተላለፉት ሰርኩሮች የተፈቀደላቸው ለራሳቸውና ለቤተሰብ (2) ተሽከርካሪ ቢሆንም 3፣ 4፣ 5 እና ከዛም በላይ (ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸው፣ ለሹፌሮቻቸው፣ ለአጃቢዎቻቸው፣ በተጠባባቂነት የሚያዝ ተሽከርካሪ እና ወዘተ.) የሚመደብ መሆኑና የሚይዙት የተሽከርካሪ ዓይንትም በሰርኩላሩ መሰረት ለከተማ የሚሆንና ነዳጅ ቆጣቢ (አውቶሞቢል) አለመሆኑ፡ **(ዝርዝሩ በአባሪ 4 ተያይዟል)፡፡**

ለማሳያ፡-

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General



- **በነሃሴ 2011 ዓ.ም በቁጥር መ-899 የተሻሻሉ የ1997 እና 2004 ዓ.ም መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ በሚኒስትሮች ም/ቤት የተዘጋጀ ሰርኩላር በዋና ዳይሬክቶር የሚመሩ የመንግስት ተቋማት ለዋና ዳይሬክተርና ለም/ዋና ዳይሬክተር አንድ አንድ ተሽከርካሪ ብቻ የተፈቀደ ቢሆንም ባለስልጣኑ ጭምር 2 እና ከ2 ባላይ እየተጠቀሙ መሆናቸው፤**

ለማሳያ፡-





ለማሳያ፡-



በናሙና ተመርጠው ለታዩ የፌደራል መ/ቤቶች ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር ከተደረገ ቃለ-መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

25. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ ላይ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ

- ተቋማት ያላቸውን የተሽከርካሪ መረጃ እንደሌላቸው/ እንደማያውቁ/ እና ለቀጣይ በፍሊት ማኔጅመንት የሚስተካከል መሆኑን፣
- የተሽከርካሪ ምደባ የተቋማት ስራ እንደሆነ እና 6 እና 7 ተሽከርካሪዎች የሚይዙ

ኃላፊዎች እንዳሉ መረጃ እንዳላቸው ነገር ግን ከባለስልጣኑ በላይ በሚንስትር ደረጃ በመሆናቸው መከልከል እንደማይችሉ እና መመሪያው ሲሻሻል የሚታይ መሆኑን፤

- በአዲሱ አዋጅ 1333/2016 በታህሳስ 2017 ኦዲት በሚያከናውንባቸው የፌደራል መ/ቤቶች ላይ በተሽከርካሪ ስምሪት መመሪያ 32/2004፣ በጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ነሃሴ 2011 እና ህዳር 2012 ዓ.ም በተላለፉ ሰርኩላሮችና በሌሎችም ኦዲት የሚያከናውን መሆኑን የሓረመያ ዩኒቨርሲቲ የኃላፊ የቤተሰብ ተሽከርካሪ የመዘዋወሪያ ቅፅ /ነዳጅ የሚያሳይ ማስረጃ አለመገኘቱ አንድ ግኝት ያገኙ መሆኑን፣

ገልጸዋል፡፡

26. የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ባለሥልጣኑ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በየተቋማቱ ክትትል ሲያደርግና የህጋዊነት ኦዲት በሚያከናውንበት ወቅት እንዚህን ችግሮች ማሳየትና የመፍትሔ አቅጣጫ ማስቀመጥ ያለበት እና ከባለሥልጣኑ አቅም በላይ ናቸው የተባሉትን ችግሮች ለይቶ በማውጣት ተጠሪ ለሆነበት ሚነቢስቴር መ/ቤት ባለማሳወቁ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

27. ባለስልጣን መ/ቤቱ በሚያደርገው የክትትልና የቁጥጥር ሥራና ህጋዊነት ኦዲት ጉዳዮቹን በመለየት የመፍትሔ ሃሳብ አለ፡፡ ማለቱ እና አስቸጋሪ የተባሉ ጉዳዮችን ለገንዘብ ሚኒስቴር አለማሳወቁ እንደምክንያት ተወስዷል፡፡

28. በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች እና ነዳጅ አመዳደብ እና አጠቃቀም የበላይ ኃላፊዎችም ጭምር ቁጥጥር ባለማድረጉ በመንግስት ንብረት ከፍተኛ የንብረት ብክነት እንዲሁም የተሽከርካሪ እጥረት ያለባቸው ተቋማት በመኖራቸው ፍትሃዊ ያልሆነ አጠቃቀም እንዳይስተካከል አድርጓል፡፡

ተሽከርካሪዎች፣ ነዳጅ እና ቅባት፣ በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፡

29. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች እና ነዳጅ፣ ቅባት፣ በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

ይገባል፡

30. ይሁን እንጂ በባለስልጣኑ በኦዲት ወቅት፡-

- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ በፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎች እና የነዳጅ አጠቃቀም ላይ ክትትል እና ቁጥጥር እያደረገ አለመሆኑ፤
- ❖ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች እና ነዳጅ፣ ቅባት፣ በተገቢው መንገድ ጥቅም ስለመዋላቸው ለአሰራር መነሻ የሚሆን (መመዘኛ፣ የንብረት አስተዳደር ቴክኖሎጂ፣) እንዲደግፋቸው ለባለስልጣን መ/ቤቱ ጠይቀው መልስ ያልተሰጣቸው መሆኑን መገለጻቸው (ለማሳያ፡- ፍትህ ሚ/ር፣ ውሃና ኢነርጂ ሚ/ር፣)፤
- ❖ የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪ እና የነዳጅ አጠቃቀም ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት እንዲዘረጉ ባለስልጣን መ/ቤቱ በመመሪያ 32/2004 ዓ.ም ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ያለበት ቢሆንም ይህንን ያላደረገ መሆኑ፤
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ በ2014፣ 2015ና 2016 በጀት ዓመት በመንግስት ሀብትነት ተመዝግበው የሚገኙ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች የሚገኙበት ደረጃና ይዞታ በጥናት በመለየት ለሚመለከተው አካል የመፍትሄ ሀሳብ ለማቅረብ እቅድ ቢይዝም ያላከናወነ መሆኑን፣
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ አዋጅ ቁጥር 649/2001 የፌደራል መ/ቤቶች ንብረት (የተሽከርካሪና ነዳጅ) አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊነት፣ አያያዝ፣ ስምሪት፣ ጥገናና መለዋወጫ፣ የነዳጅና ቅባት አጠቃቀም መቆጣጠርና ሙያዊ ድጋፍ እና ንብረትን ብክነት ለመታደግ ቁጥጥር (supervision) ለማድረግ በ2014 ዓ.ም በሀዳርና የካቲት ለስድስት መ/ቤቶች የተፃፍ ደብዳቤዎች ቢገኙም የቁጥጥር ሥራው ስለመከናወኑ (supervision) የቀረበ ሪፖርት ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀ ድረስ ለኦዲት ስራው አለመቅረቡ እና የቁጥጥር ስራው ስለመቀጠሉም የቀረበ ሰነድ አለመኖሩ፤
- ❖ በናሙና ተመርጠው የታዩ የፌደራል መ/ቤቶች የነዳጅ ማስረጃዎች ለመገምገም በሚያመች ተሟልተውና ተደራጅተው እያስቀመጡ አለመሆኑ፤

ከተከለሱ ማስረጃዎች፣ በናሙና ተመርጠው ለታዩ የፌደራል መ/ቤቶች ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር ከተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General

31. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ እና የነዳጅ፣ የቅባትና ዘይት አጠቃቀም/ የሚሰራጭበት (ለምሳሌ፤ የስምሪት ዕቅድና የውጤት መመዘኛ ዝርዝር አፈፃፀም/ ተጨማሪ ዝርዝር የውስጥ ቁጥጥር) ስርዓት እንዲዘረጉ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ያላደረገ መሆኑን፣ በዚህ ዙሪያ ሰፊ ችግር መኖሩን፣ ነገር ግን ለቀጣይ አሁን በሙከራ ትግበራ ላይ ባለው ፍሊት ማኔጅመንት ተግበራዊ ሲሆን የእነዚህንም መረጃዎች ስለሚያካትት ችግሩ እንደሚፈታ ገልጸዋል፡፡

32. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች እና ነዳጅ፣ ቅባት፣ በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር አለማድረጉ የሰው ኃይል አለሟሟላት እና የአሰራር ስርዓቱ በቴክኖሎጂ የዘመነ አለመሆኑ ለችግሩ እንደምክንያት ተወስደዋል፡፡

33. በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች እና ነዳጅ በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የውስጥ አሰራር እንዲኖራቸው ድጋፍና ቁጥጥር ባለማድረጉ ጠንካራና ወጥ የሆነ አሰራር እንዳይኖራቸው እና ትክክለኛ የወጣውን የነዳጅና ቅባት ወጪን ማወቅን አስቸጋሪ አድርጓል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

የነዳጅ እና የተሽከርካሪ አጠቃቀም ግምገማና ግብረ-መልስ የሚሰጥ መሆኑን በተመለከተ፡-

34. ባለስልጣን መ/ቤቱ በፌደራል መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም እና የተሽከርካሪ ስምሪትና አያያዝ ግምገማና ግብረ-መልስ የሚሰጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

35. ይሁን እንጂ በባለስልጣኑ በኦዲት ወቅት፡-

- ባለስልጣን መ/ቤቱ የተሽከርካሪ ስምሪትና አያያዝ እንዲሁም የነዳጅ አጠቃቀምን አስመልክቶ ግምገማ የሚያደርግበትና ግብረ-መልስ የሚሰጥበት ሥርዓት ያለዘረጋ መሆኑ፤
- በኦዲቱ በናሙና የታዩ የፌደራል መ/ቤቶች አልፎ አልፎ በሚልኩት የነዳጅና ጥገና ወርሃዊ ሪፖርት ሲልኩም ትክክል ነው ወይ አይደለም፣ የጥገና ድግግሞችና ወጪ በዝቷል እና ወዘተ. የሚል ባለስልጣን መ/ቤቱ ግብረ-መልሶች

እንደማይሰጣቸውና መላክ እያቆሙ መሆኑን መግለጻቸው፤

- ❖ የፌደራል መ/ቤቶች ጊዜቸው የማይሰራ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት እየሰጡ መሆኑ፡-ለማሳያ የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በ2015 ዓ.ም ለበርካታ ወራት ለምሳሌ፡ መሰከረም 8 ተሽከርካሪዎች፤ ኅዳር 8 ተሽከርካሪዎች፤ ጥር 8 ተሽከርካሪዎች፤ በመጋቤት 7 ተሽከርካሪዎች፤ ግንቦት 7 ተሽከርካሪዎች፤ ሰኔ 11 ተሽከርካሪዎች፤ ሓምሌና ነሃሴ 3 ተሽከርካሪዎች፤
- ❖ በጂንካ ዩኒቨርሲቲ በትብብር በማለት ታርጋ ቁጥሩ ላልተገለጸ መኪና እና ለምን ስራ እንደዋለ በማይታወቅ በተለያየ ወራት ነዳጅ መጠን 3,170 ሊትር በትብብር በማለት ብቻ እየተገለጸ ሪፖርቱ ለባለስልጣኑ የሚላክ ቢሆንም ባለስልጣን መ/ቤቱ የተላከለትን ወርሀዊ የነዳጅ አጠቃቀም ሪፖርት ተመልክቶ ለመ/ቤቱ ግብረ-መልስ ያልሰጠ መሆኑ፤
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ ግምገማና ግብረ-መልስ ባለመስጠቱ በአሰራር ላይ የሚፈጠሩ ክፍተቶችን ለይቶ እንዲያስተካክሉ አለማድረጉ፤ በናሙና ተመርጠው የታዩ መ/ቤቶችም ስራዎች በተለምዶ የመስራት ሁኔታ መኖሩን የገለፁ መሆኑ፤
- ❖ በፌደራል መ/ቤቶች የስምሪት ስራ ክፍል የሰው ኃይል ያልተመደበላቸው፣ በአንድ ባለሙያ ከሌላ ስራ ጋር ደርበው በወክልና የሚሰሩ፣ በመሰረታዊ ጠቅላላ አገልግሎት ኃላፊ ብቻ የሚሰሩ፣ በአንድ ባለሙያ ብቻ የሚሰሩ መ/ቤቶች እንዳሉ (ለማያ:- ፌደሬሽን ም/ቤት፣ ኦዲት ቦርድ) እና የስራ ጫና ያለው ሆኖ ትኩረት ያልተሰጠው የስራ ክፍል መሆኑን፤ ባለስልጣኑ የመንግስት ንብረት በአግባቡ ለማስተዳደር፣ ብክነትን ለመከላከልና ለማስቀረት በየተቋማቱ በየጊዜው ክትትልና ቁጥጥር አለማድረጉን፤ ለበላይ ኃላፊዎች ግምገማና ግብረ-መልስ እየሰጠ ይህንን እንዲያስተካክሉ አለማድረጉን፤

ከተከለሱ ማስረጃዎች፣ በናሙና ተመርጠው ለታዩ የፌደራል መ/ቤቶች ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር ከተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

36. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅቀ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪና የነዳጅ ሪፖርት በወቅቱ ባለማቅረባቸው እና አሰራሩ በቴክኖሎጂ ባለመታገዙ ምክንያት የግምገማና ግብረ-መለስ ስርዓት አለመዘርጋቱን፣ ግምገማና ግብረ-መለስ እየተሰጠ

አለመሆኑንና ቢገለፅም በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ የተሰጠ ምልሽ የተሽከርካሪ ነዳጅ፣ ቅባት አጠቃቀምና ጥገና ወጪ ሪፖርት ለባለስልጣን መ/ቤቱ ከማድረግ አኳያ አብዛኞቹ ተቋማት ሪፖርታቸውን በየወሩ እና በየሩብ ዓመቱ የሚልኩ ቢሆንም አንዳንድ ተቋማት ላይ ክፍተት እንዳለ ማረጋገጣቸውና ክፍተቱ አሁን በሙከራ ትግበራ ላይ ያለው በፊሊት ማናጀመንት ተቋማት ሁሉንም ሥራ በሲስተሙ ስለሚሰሩ በየጊዜው መረጃው ስለሚገባ ችግሩ እንደሚፈታ ገልፀዋል፡፡

37. ባለስልጣኑ በፌደራል መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም እና የተሽከርካሪ ስምሪትና አያያዝ ግምገማና ግብረ-መልስ የሚሰጥበት ዘመናዊ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ የአደረጃጀት ችግር የሰው ኃይል አለሚሟላት፣ ለችግሩ በዋነኛነት እንደምክንያት ተወስዷል፡፡

38. በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች እና ነዳጅ አጠቃቀም ላይ የግምገማና ግብረ-መልስ ስርዓት ባለመዘርጋቱ፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ባለመስጠቱን ወርሃዊ የነዳጅ፣ የጥገና እና ዓመታዊ የተሽከርካሪ ሪፖርት እንዳይልኩ ዓመታዊ የጥገና ድግግሞሽና ከፍተኛ ወጪ እንዲኖር፣ አሰራሮች እየተሻሻሉ እንዳይሄዱ አድርጓል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

የፌደራል መ/ቤቶች የነዳጅና የጥገና እቃዎች ወጪ ወርሃዊ ሪፖርት እንዲያቀርቡ መድረጉን በተመለከተ፡-

39. የፌደራል መ/ቤቶች ተጠቅመዋል ተብሎ የሚቀርበው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው ኪ.ሜ ጋር እየተመዘገበና የቅባት፣ የዘይት፣ የጥገ እና የመለዋወጫ እቃዎች ወጪ በየወሩ ለባለስልጣን መ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ሊያደርግ እና የነዳጅ መቆጣጠሪያ ጌጅ መኖሩን /መስራቱን/ ሊከታተል ይገባል፡፡

40. ይሁን እንጂ በባለስልጣኑ በኦዲት ወቅት ፡-

❖ በ2014 በጀት ዓመት ወርሃዊ የተሽከርካሪ ነዳጅ ቅባትና መለዋወጫ ሪፖርት እንዲልኩ ለማድረግ 187 መ/ቤቶች ታቅዶ 89 /47.6% / ብቻ የተከናወነ መሆኑ እና በ2015 እና 2016 በዚህ ዙሪያ የተሰራ ስለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ አለመኖሩ/ አለመቅረቡ፣ ባለስልጣኑ ክትትልና ቁጥጥር አድርጎ ግብረ-መልስ እየሰጣቸው አለመሆኑ እና ሲልኩ የነበሩትም መላክ ያቆሙ መኖራቸው፤ (**ዝርዝሩ**

በአባሪ 5 ተያይዟል)

- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ አልፎ አልፎ ሪፖርቱ በሚልኩ የመንግስት መ/ቤቶችም አፈጻጸማቸውን እየገመገሙ እየላኩ ስለመሆኑ ክትትል እና ቁጥጥር እያደረገ አለመሆኑን፡

ለማሳያ፡-

- ❖ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚ/ር በጥቅምት/2016 ዓ.ም በላከው ወርሃዊ የነዳጅ ቅባት ዘይት ሪፖርት ላይ የታርጋ ቁጥር 4-17743 320 ሊትር፣ ታርጋ ቁጥር 4-13626 240 ሊትር፤ በህዳር 2016 ዓ.ም የታርጋ ቁጥር 4-32658 160 ሊትር ተሞልቶልቶላቸው በተሞላላቸው ነዳጅ እንቅሳቃሴ እንዳላደረጉ /መኪናው በተሞላለት ነዳጅ ምን እነደሰራ /መሰክ ወጥቶ ይሁን ወይ /ምን አገልግሎት እንደሰጠ አይገልፅም ባለስልጣኑም በዚህ ላይ ግብረ መልስ ያልስጠ መሆኑ፤
- ❖ ባለስልጣኑ የተሽከርካሪ ነዳጅ ቅባትና መለዋወጫ ወርሀዊ ሪፖርት የማይልኩትን ተቋማት እየተከታተለ እንዲልኩ ያላደረገ መሆኑ፣
- ❖ በናሙና ከታዩ ተቋማት ውስጥ በ2017 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሂሳብ ኦዲት ቦርድ ሪፖርት መላክ የጀመረ መሆኑ፣ ሪፖርት ከማይልክ ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እንዲሁም ሪፖርት በተደጋጋሚ ልኮ የተመለሰበትና መላክ ያቆመ እንዱስተሪ ሚኒስቴር በቀረበላቸውና ቃለ-መጠይቅና በተከለሱ ሰነዶች የታወቀ መሆኑ፣
- ❖ ገንዘብ ሚኒስቴር የፌደራል መ/ቤቶችን የተሸከርካሪ ስምሪት፣ አያያዝ፣ የጥገና እና የነዳጅ ከ2014 እስከ 2016 በጅት ዓመት የተያዘ በጅት እና ጥቅም ላይ የዋለ በጀት ማስረጃ እንዲያቀርቡ በባለሥልጣን መ/ቤቱም ጭምር ተጠይቀው ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያላቀረቡ መሆኑ፣
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎችን የነዳጅ መቆጣጠሪያ ጌጅ እንዳላቸውና በትክክል መስራቱን እየተቆጣጠሩ ስለመሆኑ በየወቅቱ የማያረጋገጥ መሆኑ፡
- ❖ መ/ቤቶች በላኩት ወርሀዊ የነዳጅ አጠቃቀም ሪፖርት ላይ ጌጃቸው የማይሰራ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት እየሰጡ ስለመሆናቸው ቢገልጽም በባለስልጣኑ እንዲያስተካክሉ አለማድረጉ ለማሳያ፡- ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ታርጋ ቁጥር 4-02416፣ 4-02430፣ 4-07813፣ 4-02437፣ 4-10687፣ 4-08441፣ 4-08817፣ 4-1225፣ 4-07812፣ 4-106732 መኪኖች ጌጃቸው የማይሰራ ለ12 ወራት አገልግሎት የሰጡ መሆኑ፤

❖ ጅንካ ዩኒቨርሲቲ ለተሽከርካሪዎቹ የሚሞላው ነዳጅ በወር ውስጥ ከ700 ሊትር እስከ 1,050 ሊትር እየተሞላ መሆኑ እና ከፍተኛ የነዳጅ ፍጆታ እንደሚጠቀሙ የሚያሳይ ቢሆንም ባለስልጣኑ ለምን ከፍተኛ እንደተጠቀሙ ያልተነተነ እና እንዲያስተካክሉ ያላደረገ መሆኑ፤

በናሙና ተመርጠው ከታዩ የፌደራል መ/ቤቶች ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር ከተደረገ ቃለ-መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

41. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች ለማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅ፣ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ፡- የፌደራል መ/ቤቶች የነዳጅ እና ጥገና ወርሃዊ ሪፖርት እና አፈፃፀማቸውን እየገመገሙ እንዲልኩ ክትትል አለማድረጋቸውን፤ ግምገማና ግብረ-መልስ የማያደርጉ ቢሆንም ነገር ግን በህጋዊነት ኦዲት ወቅት ጌጃቸው ስለ መስራቱ የ2 እና 3 ተሽከርካሪዎች የሚታይበት ሁኔታ መኖሩን እና ከላይ የተገለፁ ክፍተቶች በቀጣይ የፌሊት ማናጅመንት ስርዓት ተግባራዊ ሲሆን የሚፈታ ይሆናል በማለት ገልፀዋል፡፡

42. የፌደራል መ/ቤቶች በአግባቡ መጠቀማቸውን የሚያሳይ የነዳጅ መጠን ከሸፈነው ኪ.ሜ ጋር እየተመዘገበና የቅባት፣ የዘይት፣ የጥገና እና የመለዋወጫ እቃዎች ወጪ በየወሩ ለባለስልጣን መ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያቀርቡ አለማድረጉ እና የነዳጅ መቆጣጠሪያ ጌጅ መኖሩን መስራቱን አለመከታተሉ የዘመነ አሰራር (የተሽከርካሪ የመረጃ ቋት) አለመኖሩ እና ባለው የሰው ኃይል እንዲልኩ ጥረት አለማድረጉ ለችግሩ እንደምክንያት ተወስደዋል፡፡

43. በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎች እና ነዳጅ አጠቃቀም ወርሃዊ ሪፖርት እየገመገሙ እንዲልኩ ክትትል ባለማድረጉ ነዳጅ በአግባቡ ስለመጠቀማቸው ለማወቅ እንዳይቻል እና የጥገና ፍጆታ እንዳይታወቅ ያደርጋል፡፡

የተሽከርካሪዎችና ነዳጅ አጠቃቀም የህጋዊነት ኦዲት መድረጉንና ሪፖርት መቅረቡን በተመለከተ፡-

44. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌዴራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎችና ነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ሁሉንም ተቋም ለማዳረስ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ የህጋዊነት ኦዲት ሊያደርግ እና ለሚመለከተው አካል ውጤቱን ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

45. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት በባለስልጣኑ ፡-

❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ ያከናወናቸውን የህጋዊነት ኦዲት ውጤት ተጠሪ ለሆነበት ለገንዘብ ሚ/ር ስለመላኩ የሚያሳይ ማስረጃ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ከሦስት መ/ቤት ወጪ ያላቀረበ መሆኑ፤

❖ የባለስልጣኑ የኦዲቱ ግብረ-መልስ ኦዲት ከተደረጉ በኋላ ለሚመለከታቸው ስራ ክፍሎች የማይደርሳቸው ተቋማት መኖራቸው (ለምሳሌ፡- ቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል፣ስታትክስ አገልግሎት፣)፣ ይህንን የክትትል ኦዲት በሚያደርግበት ወቅት እንዲታረም አለመደረጉ እና የኦዲት ክፍተቱ/ ግኝቱን ሰለመፈታቱ ቁጥጥር ማያደርግና ተቋማትም የወሰዱትን እርምጃ የማያሳውቁት መሆኑ፤

በናሙና ተመርጠው ለታዩ የፌደራል መ/ቤቶች ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር ከተደረገ ቃለ-መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

46. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅቀና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ የህጋዊነት ኦዲት ጥራትና ሽፋን እንደሚቀረው፣ የኦዲት ግብረ-መልሱ ለኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ለሚመለከታቸው የስራ ክፍል (ለመሰረታዊ ጠቅላላ አገልግሎት/ ለስምሪት ስራ ክፍሎች) መድረሱን በባለሙያ እጥረት ክትትል እንደማያደርጉ፤ ነገር ግን የኦዲት ሪፓርቶችን ለገንዘብ ሚ/ር እና ለፓርላማ እንደሚላክ ገልፀዋል፡፡

47. የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ የኦዲት ሪፖርቶች ለገንዘብ ሚ/ር ግልባጭ የተደረገው በህዳር 2017 በጀት ዓመት የወራቤ ዩኒቨርሲቲና ትምህርትና ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ብቻ እና በታህሳስ 2017 የሓረማያ ዩኒቨርስቲ ብቻ በመሆኑ፤ ለፓርላማ ሪፖርቱ ስለመላኩና በምን አይነት የህግ አግባብ ለምክር ቤቱ የኦዲት ሪፖርቱን እንደሚልኩ የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ፤ እንዲሁም የክትትል ኦዲት በሚደረግበት ወቅት የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች በኦዲቱ የተሰጣቸው ግብረ-መልስ እነሱ ጋር ስለመድረሱ የማጣራት ስራ የማይሰራ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

48. በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች እና ነዳጅ አጠቃቀም ላይ የህጋዊነት ኦዲቱ ጠንካራና ውጤታማ ባለመሆኑ እና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ባለመቅረቡ እርምጃ እንዳይወሰድና ክፍተቶቹ እንዳይፈቱ

ያደርጓል፡፡

የተሽከርካሪ አጠቃቀምን መቆጣጠርያ የሥምሪት አስተዳደር (Fleet Management ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፡-

49. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪና የነዳጅ አጠቃቀምን ለመከታተልና ለመቆጣጠር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አገር አቀፍ የሥምሪት አስተዳደር (Fleet Management) ሥርዓት ሊዘረጋና ሊተገብር ይገባል፡፡

50. ይሁን እንጂ በባለስልጣኑ በኦዲት ወቅት፦

- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አገር አቀፍ የሥምሪት አስተዳደር (Fleet Management) ሶፌት ዌር በባህርዳር ዩኒቨርስቲ አመካኝነት በጥቅምት 30/ 2015 የአንድ ዓመት ውል ተገብቶ እና ለምቶ በ13 መ/ቤቶች (ለማሳያ፡- ጤና ሚ/ር፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ስታስቲክስ አግልጋሎት፣ ግብርና ምርምር፣) የሙከራ ስራ (የተሽከርካሪዎቻቸውን መረጃ) አደራጅቶው ለባለስልጣኑ ለመላክ የሙከራ ስራውን ያስቸገራቸው መሆኑን መግለጻቸው፣ (በናሙና የተመረጡት **የ13 መ/ቤቶች ዝርዝር በአባሪ 7 ተያይዟል**)፡፡
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ የተሽከርካሪ አያያዝ እና የነዳጅ አጠቃቀም ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሥምሪት አስተዳደር (Fleet Management) ሥርዓት ለመዘርጋት በመጀመሪያ የመነሻ (የአዋጭነት) ጥናት ያላደረገ መሆኑ፤
- ❖ የሥምሪት አስተዳደር (Fleet Management) ሥርዓት ከመቼ ዓ.ም. ጀምሮ እየታቀደ የመጣ መሆኑን (ሂደቱም ከመቼ እንደጀመረ) በግልፅ የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ሰራ ያልቀረበ መሆኑ፤
- ❖ ባለስልጣኑ ከተሽከርካሪ ከምዝገባ በዘለለ በሙከራ ያለው አፈፃፀም እየገመገመ ወደ ተግባር አለማስገባቱን በናሙና ተመርጠው በአካል በመስክ የታዩ መ/ቤቶች የገለጹ መሆኑ፣
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ የለማውን ስርዓት ሙከራ ለማድረግ በናሙና 13 መ/ቤቶች የተመረጡ ሲሆን ለእነርሱም ቢሆን ሶፍት ዌሩ በስምሪት አከባቢ ያሉት ባለሙያዎች ስልጠና ከመስጠት በዘለለ ስራ ላይ አለመዋሉ ተቋማት መኖራቸው፣
- ❖ ስልጠናውም የሚሰጠው ለስምሪት ባለሙያ ብቻ እንጂ ለሚመለከታቸው ለሁሉም ማለትም (ለጠያቂ፣ ፈቃጅና አፅዳቂ) ስልጠና ያልተሰጣቸው መሆኑ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

እና

- ❖ በባለስልጣን መ/ቤቱ በኩል ዘመናዊ ውጤታማና ጂ.ፒ.ኤስ ያካተተ የተሸከርካሪና የነዳጅ አስተዳደር ስርዓት ለመዘርጋትና ለመተግበር በሂደት ላይ መሆኑን በናሙና ከተመረጡ 13 መ/ቤቶች ውጪ ለሆኑት የመንግስት መ/ቤቶች ግንዛቤ አለመፍጠሩ፣
- ❖ እንዲሁም መ/ቤቶቹ የራሳቸው የንብረት አስተዳደር ሶፍት ዌር እያለሙ ያሉ መ/ቤቶች ባለስልጣን መ/ቤቱ እንዲያይላቸውና በስልጠናም ድጋፍ እንዲደረግላቸው ጥያቄ ቢያቀርቡም በባለስልጣኑ ምላሽ ያላገኙ ስለመሆኑ ፍትህ ሚኒስቴር እና የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር መግለፃቸው፣
- ❖ በራሳቸው ሶፍትዌር በማዘጋጀት፣ መረጃዎች በመሰብሰብ ላይ ያሉና ለባለሥልጣኑ ያላሳወቁ መኖራቸው ለማሳያ፡ /ኢንዱስትሪ ሚ/ር፣ የኢትዮጵያ ስታስቲክስ አገልግሎት እና ከናሙናዎቹ ውስጥ ሆኖ ግን በራሱ ስርዓት እየተጠቀመ ያለው ድግሞ ጤና ሚ/ር መሆኑ፣
- ❖ በተጨማሪም የተሸከርካሪዎቻቸውንና የነዳጅ አጠቃቀም ለመከታተል ለመቆጣጠር ዘመናዊ ጂፒኤስ ለማስገጠም በሂደት ላይ ያሉ መ/ቤቶች በመኖራቸው መንግስት ሁለት ወጪ የሚያወጣበት ሁኔታ እየተፈጠረ መሆኑ፣
- ❖ በ2014 በጀት ዓመት ለፌደራል መንግስት መ/ቤቶች አገልግሎት የሚውል የፌሊት ማኔጅመንት መመሪያ ለማዘጋጀት እና የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን እንዲሰሩ እቅድ ቢያቅድም ያልተከናወነ መሆኑ፣
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ በሙከራ ካሉት ከ13 መ/ቤቶች ውጪ ለሆኑት ለሌሎቹ የፌዴራል መ/ቤቶች ስለተሸከርካሪና ነዳጅ አስተዳደር (Fleet Management ሥርዓት መረጃው እንዲኖራቸው አለማድረጉና ቅደመ ዝግጅት እንዲያደርጉ አለማደረጉን፤

በናሙና ተመርጠው ለታዩ የፌደራል መ/ቤቶች ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር ከተደረገ ቃለ-መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

51. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅቀ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ፡-

- ሥርዓቱን ከአለማው ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር ውሉ አንድ ዓመት

እንደነበረና እና /መተግበር/ ያልተጀመረ መሆኑን፣

- በናሙና ለተመረጡት ተቋማት የአሰልጣኞች ስልጠና የተሰጠ ቢሆንም በቂ አለመሆኑን፤
- እየተሰራ ያለው መሰረተ ልማት በ13 የሙከራ ስራው ተግባራዊ እንዳሆን እንቅፋት እሆነ መሆኑ፤
- የሥምሪት አስተዳደር (Fleet Management) ስርዓት ለመዘርጋትና ተግባራዊ ለማድረግ ከ2016 በጀት ዓመት ጀምሮ የታቀደ መሆኑ፤
- ያዋጭነት ጥናቱ ትልቅ ፕሮጀክት አንፀራዊ በሆነ በአነስተኛ ዋጋ መንግስታዊ ተቋም ያለማው በመሆኑ ጥናት ለማስጠናት ሲስተሙን ለማስለማት ከተከፈለው በላይ ይጠይቃል ተብሎ በመታሰቡ መሆኑን፤
- በሙከራ ያሉት 13 መ/ቤቶች የተሽከርካሪ መረጃቸውን እያስገቡ መሆኑና ነገር ግን ወደ ተግበራ ግን ያልገቡ መሆኑ፤ ሌሎች ወደ 50 ተቋማትም 45ቱ ዩኒቨርሲቲዎች በተሽከርካሪና ነዳጅ አስተዳደር (Fleet Management ሥርዓት የተሽከርካሪ መረጃቸውን እንዲልኩ ፍላጎት እንዳላቸውና ባለስልጣኑም በሚቀጥለው እቅዱ እንዳካተታቸው

ገልጸዋል፡

52. ባለስልጣኑ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች እና ነዳጅ አያያዝና አጠቃቀም ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሥምሪት አስተዳደር (Fleet Management) ሥርዓት ለመተግበር የዘረጋውን ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ መዘግየቱ እና በተቋማቱ ለዚህ የሚመጥን ባለሙያ አለማበቃት ለችግሩ እንደምክንያት ተወስደዋል፡፡
53. በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች እና ነዳጅ አያያዝና አጠቃቀም ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሥምሪት አስተዳደር (Fleet Management) ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ባለመሆኑ በተሽከርካሪና ነዳጅ አጠቃቀም ላይ እየተፈጠሩ ያሉ የአሰራር ክፍተቶች እንዳይፈቱ፣ ማስረጃዎች በአግባቡ እንዳይያዙ፣ ክትትልና ቁጥጥር ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዳይከናወን አድርጓል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

ተሽከርካሪዎች ለእያንዳንዳቸው የህይወት ታሪክ መዝገብ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ፣

54. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች ለእያንዳንዳቸው የህይወት ታሪክ መዝገብ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ መዋሉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

55. ይሁን እንጂ በባለስልጣኑ በኦዲት ወቅት፡-

- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የፌዴራል መንግስት ተሽከርካሪዎች የሚመዘገቡበትን ወጥ የሆነ የመንግስት ተሽከርካሪዎች የህይወት ታሪክ መመዝገቢያ ቅጽ 04 አዘጋጅቶ እንዲተገበር ለሁሉም ተቋማት የላከ መሆኑ፣ ነገር ግን
  - ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ለእያንዳንዳቸው ተሽከርካሪዎቻቸው የህይወት ታሪክ መዝገብ /ፋይል እያዘጋጁ መሆኑን እየተከታተለና እያረጋገጠ አለመሆኑና ቅፅ 04 ሳይሞላ (ባዶ) ፋይል እያደረጉት መሆኑ፤
  - ❖ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች የህይወት ታሪክ ፋይል መዝገብ ያልጀመሩ መኖራቸው /ለማሳያ መስኖና ቆላማ ሚ/ር፣ ገንዘብ ሚ/ር፣ የኦዲት ቡድኑ ባቀረበው ቃለ-መጠይቅና ባደረገው የሰነድ ክለሳ ለማወቅ የቻለ መሆኑ፤
  - ❖ በፌደራል መ/ቤቶች (በናሙና ተመርጠው የታዩ) ሰነድ የሌላቸው /እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ ሰነድ የሌላቸው ተሽከርካሪዎች እንዳሉ መግለጻቸው፤ መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎችን በተለያየ ምክንያት እንዲወገዱ ሲወሰን ለማስወገድ ከፍተኛ ችግር እያጋጠማቸው መሆኑን የፍትህ ሚኒስቴር እና የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር መግለጻቸው፣ (ለማሳያ፡- ፍትህ ሚ/ር፣ ዉሃና ኢነርጂ ሚ/ር፣)፤
- ❖ በናሙና ተመርጠው ከታዩ መ/ቤቶች የህይወት ታሪክ መዝገብ ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የተወሰኑ መ/ቤቶች በሶፍት ኮፒ ለማስገባት ሙከራ እያደረጉ እያረጉ ቢሆንም ተሽከርካሪዎቹ ፋይል ተከፊቶላቸው ከምርቱ (ግዢ ከተፈፀመበት ጀምሮ) የነዳጅ ማስረጃዎች (የስራ ወረቀቶች፣ የጥገናና ሌሎች ሰነዶች እስኪወገዱ ድረስ በአግባቡ አደራጅቶና አሟልተው ማስረጃ ያላደራጁ መሆኑ፤

በናሙና ተመርጠው በታዩ የፌደራል መ/ቤቶች ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር ከተደረገ ቃለ-መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

56. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ የተጠቀሱ ክፍተቶች ትክክል መሆኑናቸው ገና ያልተሰራ መሆኑ እና ይህንን ክፍተት ለመፍታት በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የለማውና በሙከራ ትግበራ ላይ ያለው የፍሊት ማኔጅመነት ተግባራዊ ሲደረግ የሁሉም የተሽከርካሪ መረጃዎች ከተገዙበት/ ጊዜ ጀምሮ ያሉ መረጃዎች በሙሉ ስለሚካተቱ ችግሩ የሚፈታ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

57. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች ለእያንዳንዳቸው የህይወት ታሪክ መዝገብ ተዘጋጅቶ አለመመዝገባቸው እና ባለሥልጣን መ/ቤቱ ይህ ሥራ ላይ መዋሉን አለመከታተሉና አለማረጋገጡን፣ ተሽከርካሪዎች ሲገዙ ወይምንም በስጦታ ሲመጡ የተሟላ መረጃ አብሮ ለተቋማት አለመላክ ዘመናዊ የተሽከርካሪዎች መረጃ አያያዝና ልውውጥ የአሰራር ስርዓት አለመኖሩና በተቋማትና በባለሥልጣኑ በተሽከርካሪዎች አስተዳደር ላይ ትኩረት ተሰጥቶ አለመሰራቱን እንደምክንያት ተወስደዋል፡፡

58. በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች ለእያንዳንዳቸው የህይወት ታሪክ መዝገብ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ አለመዋሉን ባለሥልጣን መ/ቤቱም ባለመከታተሉና ባለማረጋገጡ ተሽከርካሪዎች ያሉበት ሁኔታ በትክክል እንዳይታወቅ፣ ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የወጣ ወጪ እንዳይታወቅይህም በተደጋጋሚ ብልሽት ሲገጥም ለማስጠገን ወይም ለማስወገድ ውሳኔ ላይ ለመድረስ አስቸጋሪ ከማድረጉም በተጨማሪ በማስወገድ ወቅትም ታሪካቸው ተሟልቶ ባለመቆየቱ ትክክለኛ መረጃ ማግኘትን አዳጋች ያደረገ እና የማስወገድ ሂደቱም እንዲጓተት አድርጎታል፡፡

በተሽከርካሪ ጥገና ወቅት የተለወጡ እቃዎች በአግባቡ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ መደረጋቸውን በተመለከተ፡

59. ባለስልጣን መ/ቤቱ በተሽከርካሪ ጥገና ወቅት የተለወጡ እቃዎች በአግባቡ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ሊደረጉ ይገባል፡፡ ባለሥልጣን መ/ቤቱም እንዚህ ንብረቶች በእርግጥ በአዲስ ተቀይረው የተቀየሩት መደረጋቸውን የሚከታተልበት ስርዓት ሊዘርጋ፤ መተግበሩን ሊከታተል ይገባል::

60. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተሽከርካሪ ጥገና ሲከናወን የተለወጡ እቃዎች በአግባቡ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ማድረጊያ ቅጽ 12 አዘጋጅቶ ተቋማት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ያሠራጨ ቢሆንም ቅጹን ተቋማት ተግባራዊ ማደረጋቸውን የማይከታተል መሆኑ፤

❖ አሮጌ እቃ ገቢ እንዲያደርጉበት በባለስልጣን መ/ቤቱ የተሰራጨውን ቅጽ 12 ግልጽ አይደለም በማለት እየተጠቀሙበት አለመሆኑ፣

❖ የተቀየሩ የተሽከርካሪ ተለዋጭ ዕቃዎች እንደ አዲስ በሞዴል 19 ገቢ የሚያደርጉ እና የተወሰኑትም የራሳቸው ፎርማት ተጠቅመው ገቢ እያደረጉ መሆኑን ባለሥልጣኑ መግለጹ፤

❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ በፌደራል በመ/ቤቶች በስራ ላይ የሚውሉ የተሽከርካሪዎች የመለዋወጫ እቃዎች ወጪዎች ለመቆጣጠር የሚያስችል የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ባለስልጣኑም ጭምር እንዲኖር ድጋፍ አለማድረጉን 10 ዓመት ስትራቴጂክ መሪ እቅድ (ከ2013-2022)፣ በመስክ በተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ መ/ቤቶች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

❖ ቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል የተሽከርካሪ የጥገና ተለዋጭ እቃ ትራንስፖርት በንብረት ክፍል ሳይሆን በስምሪት ክፍል የሚቀመጥ መሆኑ፣

❖ የጥገና ፋይሎች በትክክል ፋይል መደረጋቸው ክትትልና ቁጥጥር እያደረገ አለመሆኑን፤

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ የፌደራል መ/ቤቶች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ለባስልጣኑን ከቀረበ ቃለ -መጠይቅ ለማዎቅ ተችሏል፡፡

61. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በመመሪያ ቁጥር 32/2004 ላይ ጥገናን በተመለከተ

- በ13 ቅፆች የጥገና ቅፅ እንዲኖር ቢደረግም ከዚህ ውጪ የሰሩት ስራ እንደሌለ፣
- በፌደራል መ/ቤቶች የሰው ኃይል ያልተመደበላቸው የስምሪት ስራ ክፍሎች ያሉ ቢሆንም ክትትል እንዳላደረጉ የገለፁ መሆኑ፤ ነገር ግን በነባራዊ ሁኔታ

መግለጫ ላይ ዝርዝር የውስጥ አሰራር እና የቁጥጥር ሥርዓት ለመዘርጋት በመመሪያ ቁጥር 32/2004 አንቀፅ 9/3 ላይ ኃላፊነት የተሰጠው ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በመሆኑ በኦዲት ሥራ ወቅት በሚታየው ቼክሊስት ዝርዝር ውስጥ የሚካተት እና ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑ፤ ያገለገለ የጥገና ተለዋጭ እቃ ልክ እንደ አዲስ እቃ በሞዴል 19 ሲቆረጥ /ገቢ ሲደረግ፡ ክፍያ ለማስፈፀም ለሂሳብ ክፍል የሚሄደው ተለዋጭ እቃ ሁሉም ገቢ ላይሆኑ ስለሚችሉ ለብልሹ አሰራር በር ከፋች ሊሆኑ ስለሚችል ኦዲት/ ሱፐርቪዥን የሚያደርጉ መሆኑን፣

ገልጸዋል

62. የፌዴራል መ/ቤቶች ለተሽከርካሪ ጥገና የተለወጡ እቃዎች በአግባቡ የተመደበውን ቅጽ በመጠቀም ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ወጥ በሆነ መልክ ተግባራዊ አለማድረጋቸው እና ባለስልጣን መ/ቤቱ ቅጹ መሰረት ገቢ መደረጋቸውን አለመከታተሉ እንደምክንያትነት ተወስዷል፡፡

63. በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ለተሽከርካሪዎች ጥገና የተለወጡ እቃዎች ተመላሽ ተደርገው ገቢ መሆናቸውን ለመከታተል ተቋማት የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋታቸውን እና የተዘጋጀውን ቅጽ መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ የተዘረጋው ስርዓት በአግባቡ እየሰራ መሆኑን ካልተረጋገጠ ተቀይረዋል ተብለው ገንዘብ የተከፈላባቸው ንብረቶች በትክክል መቀየራቸውን ማረጋገጥ አዳጋች ከማድረጉም በላይ የተቀየሩ ዕቃዎችን እንደ አዲስ የተገዙ በማስመሰል ገቢ በማድረግ ለህገ-ወጥ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

የፌዴራል ተቋማት የተሽከርካሪዎች ዓመታዊ የመረጃ ሪፖርት ማቅረባቸውን በተመለከተ

64. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ለሚጠቀሟቸው ተሽከርካሪዎች ሙሉ መረጃ አመታዊ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት የተሽከርካሪ መረጃ ሪፖርት ባላቀረቡ ተቋማት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

65. ይሁን እንጂ በባለስልጣኑ በኦዲት ወቅት ፡-

❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ዓመታዊ የተሽከርካሪ መረጃዎች

በማይልኩ ተቋማት ላይ አስተዳዳራዊ እርምጃ እየወሰደ አለመሆኑ፤

❖ በ2014 በጀት ዓመት የፌደራል መ/ቤቶች ዓመታዊ የተሸከርካሪ መረጃ እንዲያቀርቡ 187 ታቅዶ 70 (37%) ብቻ ሪፖርት ያቀረቡ መሆኑ፣

❖ በ2015 በጀት አመት ዓመታዊ የተሸከርካሪ መረጃ የፌደራል መ/ቤቶች እንዲያቀረቡ 169 ታቅዶ 79 ብቻ ሪፖርት ያቀረቡ አፈጻጸሙ 46% መሆኑ፣

❖ በ2016 በጀት ዓመት አመት ዓመታዊ የተሸከርካሪ መረጃ የፌደራል መ/ቤቶች እንዲያቀረቡ 169 ታቅዶ በአመታዊ የክንውን ሪፖርቱ ምንያህል እንደተከናወነ የማይገልጽ መሆኑ /ያልተከናወነ መሆኑ፣



የ2015 በጅት ዓመት ዕቅድ እና ክንውን

❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ ግንዛቤ ባለመፍጠሩ ዓመታዊ የተሸከርካሪ ሪፖርት ለመላክ የሚመለከተው አካል ማን እንደሆነ የማያውቁ መ/ቤቶችም መኖራቸው፤ ለማሳያ የኢትዮጲያ ሂሳብ አያያዝ ኦዲት ቦርድ፣

❖ ኢንዱስተሪ ሚ/ር የወርሃዊ የነዳጅና ጥገና እና ዓመታዊ የተሸከርካሪ መረጃ ሪፖርት ለባለስልጣኑ ሲልክ የሚቀበል አካል ያላገኘ መሆኑና በተደጋጋሚ ሪፖርቱ ተመላሽ መደረጉን መግለጻቸው፤

❖ በናሙና ተመርጠው የታዩ እና ሌሎቹ የፌደራል መ/ቤቶች የተሸከርካሪዎችን መረጃ ወቅታዊ እያደረጉ ለባለስልጣኑ እየላኩለት አለመሆኑን መግለጻቸው፣

❖ በ2014፣ በ2015፣ በጀት ዓመት የፌዴራል መ/ቤቶች ወቅቱን ጠብቀው

የተሽከርካሪ መረጃ፣ የነዳጅ፣ ቅባትና የጥገና መለዋወጫ ወጪ ሪፖርት ኢንዲያቀርቡ ክትትልና ድጋፍ እንዲያደርግ እና ባላቀረቡት መ/ቤቶች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ቢያቅድም ያልተከናወነ መሆኑን እና በ2016 በጀት ዓመትም በዚህ ጉዳይ የተሰራ ስራ ስለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ አለመኖሩ/ አለመቅረቡ፤ **(ዝርዝሩ በአባሪ 5 ተያይዟል)**

በናሙና ተመርጠው ለታዩ የፌደራል መ/ቤቶች ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር ከተደረገ ቃለ-መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

66. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በማውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ የተገኘው ክፍተት ትክክል መሆኑና ያልተሰራ መሆኑን፣ የጥገና ድግግሞሽ ሊኖር እንደሚችል እና በቀጣይ የሚፈታ መሆኑን፣ በአዋጅ 649/2001 እርምጃ ለመውሰድ በሚያስችል በግልፅ ያልተቀመጠ መሆኑና የህጋዊነት ኦዲት የሚያደርጉ መሆኑን ነገር ግን እርምጃ የማይወስዱ መሆኑን አሁን ግን የፊሊት ማናጀመንት ስርዓት ሲተገበር እራሱ ሪፖርት የሚያወጣ በመሆኑ ችግሩ በዛ የሚፈታ ይሆናል በማለት ገልፀዋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

67. ባለስልጣኑ የፌደራል መ/ቤቶች ለሚጠቀሟቸው ተሽከርካሪዎች ሙሉ መረጃ አመታዊ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ በተቀመጠው ገደብ መሰረት የተሽከርካሪ ሪፖርት እንዲያቀርቡ አለማድረጉ እና ባላቀረቡ ተቋማት ላይም አስተዳደራዊ እርምጃ አለመወሰዱ የመንግስት ግዥ እና ንብረት ማሻሻያና አቅም ግንባታ ሥራ ክፍል ያለው የሰው ኃይል 50 በመቶ ብቻ በመሆኑና ባለው ሰራተኛም ለመስራትም ጥረት ከማድረግ አንፃር ክፍተት መኖሩ እና የአሰራር ስርዓቱ አለመዘመኑ እንደምክንያት ተወስዷል፡፡

68. በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ለሚጠቀሟቸው ተሽከርካሪዎች ሙሉ መረጃን የያዘ አመታዊ ሪፖርት በተቀመጠው ገደብ ለባለሥልጣኑ ባላቀረቡ ተቋማት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ባለመውሰዱ መረጃው እንዳይቀርብና የተሽከርካሪ መረጃ በአግባቡ እንዳይያዝ አድርጓታል፡፡

የተሽከርካሪዎችን የጥገና አገልግሎት ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን ማድረጉን በተመለከተ፤

69. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎችን የጥገና አገልግሎት ወጪ

ቆጣቢ እንዲሆን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

70. ይሁን እንጂ በባለስልጣኑ በኦዲት ወቅት፡-

- በ10/8/2011 ዓ.ም ከገንዘብ ሚ/ር ለባለስልጣኑ በተፃፈለት የተሽከርካሪ ጥገና ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ እንዲሆን በሚኒስትሮች ም/ቤት በ18/12/2010 በቁጥር በጠ1/6/2 በተፃፈው ደብዳቤ ወጪ ቆጣቢ መመሪያ የተሽከርካሪ ጥገናም እንደማንኛው ግዥ በጨረታ መሆን እንዳለበትና በትልልቅ የተሽከርካሪ አስመጪ ኩባንያዎች በቀጥታ ስምምነት ጥገና በማድረግ የሚወጣውን ወጪ መቀነስ እንዳለበት የተገለፀ ቢሆንም በናሙና የታዩ የፌደራል መ/ቤቶች ብዙዎቹ ባለስልጣኑም ጭምር ከአስመጪ ኩባንያዎች በቀጥታ ግዥ ጥገና እያደረጉ መሆኑ፤

ማሳያ፡-

- ❖ ትምህርት ሚ/ር በጥቅምት 15/2016 ዓ.ም በከፍተኛ አመራር ስብሰባ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ጥገና ኮንትራት በቀጥታ ግዥ ከፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት እንዲፈፀም እና በቀን ታህሳስ 26/2015 በቁጥር 25/444/836/5 በተላለፈ ማንዋል ክፍል ሶስት 3.1.1 ተሽከርካሪዎች ብልሽት ሲያጋጥማቸው በቅድሚያ በቀጥታ አስመጪ ካምፓኒዎች የሚቀበሉአቸው ከሆነ በአስመጪያቸው እንዲጠገኑ የሚል በመሆኑ የተጠቀሟቸው የጥገና ዘዴዎች ያለጨረታ መሆኑ፣
- ❖ በናሙና የታዩ መ/ቤቶች ብዙዎቹ ያለጨረታ በቀጥታ ግዥ ከአስመጪዎች የሚያስጥግኑ መ/ቤቶች መሆናቸው ለምሳሌ (ኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝ ኦዲት ቦርድ፣ መቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲ፣ መስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር፣ ገቢዎች ሚኒስቴር፣ ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር) ዝርዝራቸው **በአባሪ 5 ተያይዟል**
- ❖ እንዲሁም ባለስልጣን መ/ቤቱ የዘረጋው የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎች የጥገና አገልግሎት ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን በግልፅ ተጠያቂነትን የሚያሰፍን (እርምጃ ለመወሰድ የማያስችል) ሥርዓት አለመሆኑን እና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን በናሙና ተመርጠው የታዩ የፌደራል መ/ቤቶች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ የገለፁ መሆኑ፤
- ❖ በናሙና በታዩ የፌደራል መ/ቤቶች በኦን ላይን የሚወጡ እቃዎች እና

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

በፐርፎርማ ዝርዝር ያለው መለዋወጫ ዕቃዎች እንደማይገናኝ፤ አስመጪዋቹ ብቸኛ በመሆናቸው እስከ 2 እና 3 ዓመት የመጠበቅ ሁኔታ መኖሩ፤

❖ ኦርጅናል መለዋወጫ ዕቃዎች በጋራዦች እና በአስመጪዎች የሚፈለገውን እቃ የማግኘት ችግር እንደለና ከ1-3 ዓመት የሚቆሙ መኪኖች መኖራቸው እንዲሁም ከፍተኛ ወጪ እያስከተለ መሆኑን መግለጻቸው (ለማሳያ፡ የቅዱስ ጴጥሮስ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ ስታስቲክስ አገልግሎት፣)

❖ በፌደራል መ/ቤቶች በዓመት የጥገና ድግግሞሽ ቢኖርም ባለስልጣን መ/ቤቱ የጥገና ወጪ እያጣራና እየተቆጣጠረ አለመሆኑ እንዲሁም የጥገና ድግግሞሽ እንዲፈታ አለማድረጉ፤

ለማሳያ፡-

- ሰሌዳ ቁ. 4-25198፡- ነሃሴ 13/2014 ብር 18 149፤ ህዳር 20 እና 23/2014 ብር125,755፤ መጋቢት 30/2014 ብር 171 255፤ ግንቦት 12/2014 ብር 29 291፤ ጥቅምት 24/2015 ብር 23 922፤ መጋቢት 7/2015 ብር 106 773፤ ሰኔ 17/2016 የጥገና ወጪ ብር 72 928፤ መስከረም 10/2016 ብር 61 259፤
- የትምህርት ሚኒስቴር የተሸከርካሪ የጥገና ድግግሞችና ወጪው በሞኤንኮ ጋራዥ በቀጥታ የግዥ ጥገና፤
- የሰሌዳ ቁጥር 4-25285 በቀን 2/3/2014 ዓ.ም ብር 256,748፣ በ29/7/2014 ብር 212,949፣ በ16/10/2014 ብር 111,514፤ በ5/1/2015 ብር 35,570፣ በ7/7/2015 ብር 133,608፤
- የሰሌዳ ቁጥር 4-25276 በ7/20/2015 ብር 127,660፣ በ1/1/2016 ብር 130,777፣ በ17/10/2016 ብር 122,695፤
- የሰሌዳ ቁጥር 4-25287 በህዳር/2014 ብር 73,354፣ መጋቢት/2014 ብር 34,166፣ በመጋቢት/2016 ብር 154,813፣ በሰኔ/2016 ብር 193,139፤
- ሰሌዳ ቁጥር 4-18286 በመስከረም/2013 ብር 100,241፣ በመጋቢትና ሚያዝያ/2013 ብር 76,317፣ በነሃሴ/2013 ብር 112,602፤ በየካቲት፣ ሰኔና ነሃሴ/2014 ብር 98,420፤
- ሰሌዳ ቁጥር 4-12300 በመጋቢትና ሰኔ/2014 ብር 153,132፣ በግንቦት/2015 ብር 280,043፣ በህዳርና መጋቢት/2016 142,372፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

- ሰሌዳ ቁጥር 4-19891 በጥር/2014 ብር 111,470፣ በህዳርና መጋቢት/2016 ብር 147,531፤
- ሰሌዳ ቁጥር 4-15802 በግንቦት 2015 ብር 300,492፣ በህዳርና መጋቢት/2016 ብር 122,277፤
- በፍትህ ሚኒስቴር በጥገና ድግግሞች ከፍተኛ ወጪ መኖሩን ለማሳያ፦ ታርጋ .ቁጥር 4-24990 - ሃምሌ 24/2015 60,518 ብር፤ ሰኔ 23/2015 144 612 ብር፤ /2015 60,518 ብር፤ በግንቦት 18/2015 የመለዋወጫ ዋጋ 116,842 ብር፤ በሚዝያ 24/2015 83,257 ብር፣ ታህሳስ 27/2015 108,047 ብር፤ በጥቅምት 25/2015 ለጥገና እቃ 89,866 ብር፤
- የግብርና ባለስልጣን ተሽከርካሪ የሆነ ታርጋ ቁጥር 4-17557 ለባለስልጣኑ በላከው ወርሀዊ የነዳጅ ቅባት ዘይት ሪፖርት ላይ በጥቅምት/ 2016 ዓ.ም የተገጠመለት የመለዋወጫ ዋጋ ብር 254,305.43 በድጋሚ የካቲት/2016 ዓ.ም የተገጠመለት የመለዋወጫ ዋጋ ብር 56,974.72 መሆኑ እና ይህ ተሽከርካሪ ተደጋጋሚ የጥገና ወጪ በማስወጣቱ የተሰጠ ግብረ-መልስ /ውሳኔ አለመኖሩን፤

በናሙና ተመርጠው ለታዩ የፌደራል መ/ቤቶች ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር ከተደረገ ቃለ-መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

71. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ ጥገናን በተመለከተ የፌደራል መ/ቤቶች ስራ መሆኑ፣ የተሽከርካሪ የጥገና ድግግሞሽ መኖሩ እና የመረጃ ቋት ባለመኖሩ ክትትል እያድረጉ አለመሆኑን፣ የተለያዩ መመሪዎችና ሰርኩላሮች ተጠቃለው አዲስ በተዘጋጀው መመሪያ ላይ የተካተቱ በመሆኑ እና አሁን በሙከራ ትግበራ ላይ የሚገኘው የፍሊት ማኔጅመንት የተሽከርካሪዎች የጥገና መረጃዎችንም መያዝ የሚያካትት በመሆኑ ችግሩ በዛ ይፈታል የሚል ምላሽ ገልፀዋል፡፡

72. የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎችን የጥገና አገልግሎት ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን ለማድረግ የተላለፈው ሰርኩላር ትግበራን አለመከታተሉና በፌዴራል መ/ቤቶች ወጥ የሆነ የጥገና ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉን፣ ባለስልጣኑ የጥገና ስራውን በአግባቡ አለመከታተሉ ለችግሩ እንደ ምክንያት ተወስደዋል፡

73. በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎችን የጥገና

አገልግሎት ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን በ2011 ዓ.ም የተላለፈ ሰርኩላር አለመተግበሩ እንዲሁም ወጥ ግልጽ የሆነ የጥገና ሥርዓት አለመዘጋጀቱ ከአስመጪዎች ያለጨረታ በቀጥታ ጥገና እንዲያሰጠግኑ እና መንግስት ለከፍተኛ የጥገና ወጪ እንዲያወጣ አድርጎታል፡፡

የተሽከርካሪዎችን ሥምሪትና የነዳጅ አጠቃቀም ጥናት መድረጉን በተመለከተ

74. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎችን ሥምሪትና የነዳጅ አጠቃቀም በየጊዜው ጥናት ሊያደርግ ይገባል፡፡

75. ይሁን እንጂ በባለስልጣኑ በኦዲት ወቅት፡-

- ❖ በባለስልጣን መ/ቤቱ በመንግስት ተሽከርካሪዎችና የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የውጤታማነት መመዘኛ የዳሰሳ ጥናት አለመደረጉ፣
- ❖ ከተቋማት በየወሩ የሚላክለትን የነዳጅ አጠቃቀም ሪፖርት መሰረት በማድረግ ትንተና ያልሠራ መሆኑ
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተሽከርካሪዎች ህጋዊ ከሆነ አካል የኖርማላይዜሽን ልኬት ጥናት አስጠንቶ ተግባራዊ ማድረጋቸውን እየተከታተለ አለመሆኑ፤
- ❖ የፌደራል መ/ቤቶቹ በገለልተኛና ህጋዊ ፈቃድ በተሰጠው አካል ሳይሆን በራሳቸው ኮሚቴ የሚያስለኩ መኖራቸው/ ማሳያ፡- ግብርና ምርምር፣ ገቢዎች ሚ/ር/፣ ቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል፣ እንዲሁም ከ6 እስከ 7ና ከዛ በላይ ዓመታት ባስለኩት ልኬት የሚጠቀሙም መኖራቸው/ ለማሳያ፡- ገንዘብ ሚ/ር፣ ሓረማያ ዩኒቨርሲቲ፤
- ❖ የባለስጣን መ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ወቅታዊ የነዳጅ ፍጆታቸውን ለማወቅ የሚያስችል ኖርማላይዜሽን ልኬት አለመለካቱ በ10 ዓመት ስትራቴጂክ መሪ እቅድ (ከ2013-2022) ላይ የተገለፀ መሆኑ፤
- ❖ በፌደራል መ/ቤቶች ኖርማላይዜሽን ልኬት ሳይለካ የተሽከርካሪ ስምሪት የነበረ መሆኑ እና ለአሮጌውም ለአዲሱም በርቀቱ መሰረት እኩል ነዳጅ ይሰጣቸው እንደነበረና የነዳጅ ብክነትም እንደነበረ፣ ባለስልጣኑ ክትትል አድርጎ እንዲያስተካክሉ አለማድረጉን በናሙና የታዩ ተቋማት መግለጻቸው (ለማሳያ ፍትህ ሚ/ር፣ መሰኖና ቆላማ ሚ/ር)፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

❖ ከ2016 ዓ.ም በፊት ኖርማላይዜሽን ልኬት እንዳልነበራቸውና በ2017 በጀት ዓመት ሊኬት እያስለኩ ያሉ መ/ቤቶች መኖራቸው (ለማሳያ መስኖና ቆላማ አከባቢ ሚ/ር)፤

❖ ተሽከርካሪዎች ኖርማላይዜሽን በማስለካት ያሉና የቀሩት በሂደት ላይ /ገና ልኬት ያልተደረገላቸው ተሽከርካራች መኖራቸው፤ ለማሳያ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣/

❖ በባለስልጣን መ/ቤቱ እንዴት ኖርማላይዜሽን እንደሚሰራና እንደሚለካ ግልጽነት ያለው አሰራር አለመዘርጋቱ፤

በናሙና ተመርጠው ለታዩ የፌደራል መ/ቤቶች ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር ከተደረገ ቃለ-መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

76. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በማውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ ጥናት እንዳልተጠና፤ በጥያቄው የተነሱ ክፍተቶች ትክክል መሆናቸውን በሰው ኃይል እጥረትና ስራ ጫና ምክንያት በጥናት ያለተለዩና ያልተፈቱ ችግሮች መኖራቸውን፤ ከተቋማት ጋር የመወያየት ሁኔታ ቢኖርም አጀንዳ እና ቃለ-ጉባኤ የማይዙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም የተሽከርካሪዋቻቸው ኖርማላዜሽን ልኬት የህጋዊነት ኦዲት ግኝት ይሆንባችዋል በማለት የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ በታህሳስ 2017 በጀት ዓመት፣ የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ የ2013 ዓ.ም ማስረጃ ማቅረባቸውን፣ የኖርማላይዜሽን ልኬት በተመለከተም በበመሪው እንደአቅጣጫ የተካተተ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

77. ባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ኖርማላዜሽን ልኬት የህጋዊነት ኦዲት ግኝት የ2013 ዓ.ም መሆኑና 4 አመት ከግማሽ የሆነው በመሆኑ፤ የሐረማያ ዩኒቨርሲቲም በ2013 ዓ0.ም በኦዲት ግኝቱ በ2011 ዓ.ም የተለካ ልኬት መሆኑ ተገልፆ በታህሳስ 2017 በጀት ዓመት የ2012 ዓ.ም ልኬት እየተጠቀሙ መሆናቸው የተጠቀሰ በመሆኑ ከላይ የተዘረዘሩት የኦዲት ቡድኑ ግኝቶች የሚያጠናክር በመሆኑ፣ እርምጃም ባለመወሰዱና እሁንም ድረስ ሊኬቱ ወቅታዊ ያላደረጉ በመሆኑ፤ ከተቋማት የመወያየት ሁኔታ መኖሩን የሚያሳይ የውይይት አጀንዳና ቃለ-ጉባኤ የማይዙ በመሆኑ ምላሹን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

78. ባለስልጣኑ የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎችን ሥምሪትና የነዳጅ አጠቃቀም በየጊዜው ጥናት አለማድረጉና የሚቀርብለትን የነዳጅ አጠቃቀም ሪፖርት ላይ

ትንተና አለማድረጉና በተሽከርካሪዎችና ነዳጅ አጠቃቀም ትኩረት አመስጠቱን ለችግሩ እንደምክንያት ተወስዷል፡፡

79. በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎችን ሥምሪትና የነዳጅ አጠቃቀም አፈፃፀም ላይ በየወቅቱ የውጤታማነት መመዘኛ ጥናት ባለማድረጉ የተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀምን ለመገምገም፣ እና ለነዳጅ የሚወጣው ተሽከርካሪዎቹ ከሚሰጡት አገልግሎት አንጻር እንዳይታወቅ አድርጓል፡፡

በተሽከርካሪና ነዳጅ አጠቃቀም አስተዳደርን የቅንጅት ስርዓት መዘርጋቱ በተመለከተ፡-

80. ባለስልጣን መ/ቤቱ በተሽከርካሪ እና በነዳጅ አጠቃቀም አስተዳደርን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ የቅንጅት ስርዓት ሊዘረጋና ሊተገብር ይገባል፡፡

81. ይሁን እንጂ በባለስልጣኑ በኦዲት ወቅት፡-

- በናሙና ተመርጠው የታዩ ተቋማት ቅንጅት፣ ትብብርና አጋርነት እንደሌለ፤ ስራዎች በተናጠል የሚሰሩ መሆኑን፤ የፌዴራል መንግስቱ አመታዊ የነዳጅ አጠቃቀም ስሌት በአመት አንድ ጊዜ ኪ.ሜ. አሰሳ እየተደረገ የሚሰራበት አሰራርና የተቀናጀ ስርዓት የሌለ መሆኑን፣
- በባለስልጣን መ/ቤቱ በተሽከርካሪና በነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር ላይ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ዘላቂና ሀገራዊ ጉልህ ውጤት ሊያመጣ የሚችል የቅንጅት ስርዓትና የተስራ ስራ አለመኖሩ፤
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በመንግስት መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀምና ጥገና ላይ የምክክር መድረኮች አለማዘጋጀቱ፣

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ የፌደራል መ/ቤቶች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ -መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

82. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ የግዥና ንብረት አስተዳደር በየስድስት ወሩ የሚደረግ ወይይት መኖሩን እና በውይይቱ የሚነሳው አብዛኛው ወቅታዊ ሁኔታዎች በመሆኑ

ስለተሽከርካሪና ነዳጅ ውጤት እንዳልመጣ፣ የውይይት አጀንዳና ቃለ-ጉባኤ እንደማይያዝ ነገር ግን የጥሪ ደብዳቤዎች ማቅረብ እንደሚችሉ እና በንብረት አስተዳደር ዙሪያ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ የተሽከርካሪ አጠቃቀም እንደሚነሳ የገለፁ መሆኑ፡፡

83. የፌደራል መ/ቤቶች በተሽከርካሪ እና በነዳጅ አጠቃቀም አስተዳደርን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ የቅንጅት ስርዓት ትኩረት ሰጥቶ አለመስራቱ ለችግሩ እንደምክንያት ተወስዷል፡፡

84. በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች በተሽከርካሪ እና በነዳጅ አጠቃቀም አስተዳደርን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ የቅንጅት ስርዓት እና አጋሪነት ባለመኖሩ በንብረቶቹ ላይ ያሉ ችግሮች በጋራ እንዳይፈቱና ከብክነት እንዳይታደጉ ያደረጋል፡፡

በተሽከርካሪ እና ነዳጅ አጠቃቀም የመረጃ ሥርዓት እና መደበኛና ጠንካራ የመረጃ ልውውጥ መኖሩን በተመለከተ፡-

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

85. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል የመንግስት በተሽከርካሪ እና ነዳጅ አጠቃቀም የሚያገለግል ዘመናዊ የመረጃ መለዋወጫና አያያዝ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

86. ይሁን እንጂ በባለስልጣኑ በኦዲት ወቅት፡-

- ባለስልጣን መ/ቤቱ ሀገራዊ ዘመናዊ የተሽከርካሪ የመረጃ ቋት አለማዘጋጀቱ /አለመኖሩ እና ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ የጠፉ ተሽከርካሪዎች መኖራቸውን በናሙና ተመርጠው ከታዩ የፌደራል መ/ቤቶች በተደረገላቸው ቃለ-መጠይቅ የገለፁ መሆኑ (በናሙና ከታዩ ዓ.ም ጠቅሶ የገለፀ ፍትህ ሚ/ር መሆኑ)፣
- በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ ነዳጅ አጠቃቀምና ጥገና መረጃ ልውውጥ የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ፤
- የተሽከርካሪ ከፍተኛ የጥገና ድግግሞሽና የጥገና ወጪ መኖሩና ለማስወገድ አስቸጋሪ ሁኔታ እየተፈጠረ መሆኑ፤ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የተሽከርካሪ ታሪክ ፋይል መረጃ የሚያዝበት ሥርዓት አለመኖሩ፤
- ባለሰልጣኑ ጋር የተሽከርካሪዎች መረጃና መነሻው በራሱ በባለሥልጣኑ ጋር ቢሆንም ክትትልና ማስረጃቸውን አጠናክሮ አለመያዙ፣

❖ በ2015 በጀት ዓመት የተቀናጀ ዘመናዊ የቋሚ ንብረት አስተዳደር መረጃ ስርዓት ለመዘርጋት ቢታቀድም ያልተከናወነ መሆኑ፤

❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ በመንግስት መ/ቤቶች ስልተከናወኑ የተቋማት የተሸከርካሪ ስምሪት፣ የነዳጅ አጠቃቀምና ጥገና የሚመለከት ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት አለማቅረቡ፣

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ የፌደራል መ/ቤቶች እና የባለስልጣኑ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ -መጠይቅ ለማዎቅ ተችሏል፡፡

87. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ

- የመረጃ ቋትና የመረጃ ልውውጥ የሌላቸው መሆኑን፤
- የፍሊት ማኔጅመንት እና የተቀናጀ ዘመናዊ የቋሚ ንብረት አስተዳደር መረጃ ዝርጋታ ጅምር ስራ መኖሩን፤ በሰው ኃይል እጥረት ምክንያት የተዘረጋው ስርዓት በሚገባ እየተተገበረ ስለመሆኑ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት እየቀረበ አለመሆኑ፤
- ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የአሰራር ሥርዓት ከመገንባት አኳያ የግዥና የንብረት አስተዳደር የህግ ማዕቀፎች ዘመናዊ የአሰራ ሥርዓቶችን ተከትለው እንዲቀረጹ ከማድረግ አንስቶ በተጨባጭ የተሸከርካሪ ሥምሪትና ቁጥጥር ሥርዓቱ በሲስተም እንዲሆን ለማድረግ የe-Fleet System በ13 ተቋማት ላይ የተሸከርካሪ መረጃቸውን ማስገባት ጀምረዋል፡፡ በመቀጠልም ይህ ሥርዓት በቀጣይ በሁሉም ተቋማት ላይ ተግባራዊ የሚደረግ ይስለሚሆን ችግሩ በዚህ የሚፈታ ይሆናል በማለት

ገልፀዋል፡፡

88. የፌደራል የመንግስት በተሸከርካሪ እና ነዳጅ አጠቃቀም የሚያገለግል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ መለዋወጫና መረጃዎቹ የሚይዙበት የመረጃ ቋት ማቋቋም፣ ማኅልበት፣ መጠበቅ ወቅታዊነቱን የጠበቀ (ውጤታማነት የሚያግዝ የመረጃ ሥርዓት) አለመሆኑ እና መደበኛ የመረጃ ልውውጥ አለመኖሩ ለችግሩ እንደምክንያት ተይዘዋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

89. በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ለተሽከርካሪ እና ነዳጅ አጠቃቀም የሚያገለግል የመረጃ ቋት እና መደበኛና ጠንካራ የመረጃ ልውውጥ ባለመኖሩ የተሽከርካሪዎች መረጃ ከመነሻ ጀምሮ እንዳይያዝና እንዳይገኝ፣ የተሽከርካሪ ታሪክ፣ ነዳጅ የአፈፃፀም እና የነዳጅ አጠቃቀም ማስረጃዎች በኤሌክትሮኒክስ ለቁጥጥር አመቺ በሆነ በሆነ መልኩ እንዳይያዙ፣ የመንግስት ንብረትና ከተሽከርካሪ ጋር የተያያዙ ወጪዎች በትክክል እንዳይታወቅ አድርጎታል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General

ክፍል ሶስት

መደምደሚያ

90. ከላይ በኦዲት ግኝቶቹ ላይ እንደተመለከተው የተሽከርካሪ ስምሪት፣ አያያዝ እና የነዳጅ አጠቃቀም አፈፃፀምን በተመለከተ በመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን እና በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት የፌደራል መ/ቤቶች ላይ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም የተዘረጋው የአሠራር ሥርዓት ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ ስለመሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት ግድፈቶችና ጉድለቶች ተገኝተዋል፡

- ❖ በአዋጅ ቁጥር 1333/2016 ለማስፈጸም የሚያስችል አዲስ የግዥ መመሪያ ያልተዘጋጀ ወይንም ነባሩ መመሪያ ያልተሻሻለ /ኦዲቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ያልፀደቀ መሆኑ፣
- ❖ የበላይ ኃላፊዎች፣ ከፍተኛ ኃላፊዎችና ኃላፊዎች በሚሰጣቸው/ በሚመደብላቸው ተሽከርካሪ የሚሰጥ ወርሃዊ የነዳጅና ጥገና ወጪያቸው ሪፖርት የሚደረግበት አሰራር አለመቀመጡ፣
- ❖ በተሽከርካሪ እና ነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ 32/2004 አባሪ የተደረጉ 13 ቅጾቹም ወቅታዊ ያልተደረጉ፣ በናሙና የታዩ መ/ቤቶች አብዛኛው ቅፆችና እየተጠቀሟቸው አለመሆኑ፣
- ❖ በናሙና ከታዩ የፌዴራል መ/ቤቶች ውስጥ መመሪያ ቁጥር 32/2004፣ በ2009 ዓ.ም፣ ስለተሽከርካሪ አጠቃቀም የወጣ መመሪያ ከነማሻሻያው እንዲሁም በተለያየ ጊዜ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት እና ከገንዘብ ሚኒስቴር የሚተላለፉ ያልተገበሩ መ/ቤቶች መገኘታቸው፣
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ ለበላይ ኃላፊዎች፣ ለከፍተኛ ኃላፊዎች በህግ (በጠቅላይ ሚ/ር ጸ/ቤት በሚኒስትሮች ጽ/ቤት እና በገንዘብ ሚኒስቴር በወጡ መመሪያዎችና ሰርኩላሮች መሰረት ሥራ ላይ ስለመዋሉ አልተከታተለም አልተቆጣጠረም፣
- ❖ ለበላይ ኃላፊዎች በመመሪያና በሰርኩላር ከተወሰነው በላይ ተሽከርካሪዎች የመደቡ ተቋማት መገኘታቸው፣
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በመንግስት ሀብትነት ተመዝግበው የሚገኙ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች የሚገኙበት ደረጃና ይዞታን በጥናት አለመለየቱ፣

Office of the Federal Auditor General

- በናሙና ተመርጠው የታዩ የፌደራል መ/ቤቶች የነዳጅ ማስረጃዎች አሟልተውና አደራጅተው ያላስቀመጡ ተቋማት መገኘታቸው፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የተሽከርካሪ ስምሪትና አያያዝ እንዲሁም የነዳጅ አጠቃቀምን አስመልክቶ ግምገማ የማያደርግ መሆኑ፣
- የፌደራል መ/ቤቶች ጊጃቸው የማይሰራ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት እየሰጡ መሆኑ፣
- ወርሃዊ የተሽከርካሪ ነዳጅ ቅባትና መለዋወጫ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ የማይልኩ ተቋማት መኖራቸው፣ ለሚልኩትም ተቋማት ባለስልጣኑ ገምግሞ ግብረ-መልስ እየሰጣቸው አለመሆኑ እና ሲልኩ የነበሩትም መላክ ያቆሙ መኖራቸው፤ የማይልኩትንም እየተከታተለ እንዲልኩ አለማድረጉ፣
- በባለስልጣን መ/ቤቱ የህጋዊነት ኦዲት ተደርገው የማያውቁ የፌደራል መ/ቤቶች መኖራቸው፣ ባለስልጣን መ/ቤቱ ያከናወናቸውን የህጋዊነት ኦዲት ውጤት ተጠሪ ለሆነበት ለገንዘብ ሚ/ር ስለመላኩ የሚያሳይ ማስረጃ ተጠይቆ አለመቅረቡ፣
- በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አገር አቀፍ የሥምሪት አስተዳደር (Fleet Management) ሶፌት ዌር በባህርዳር ዩንቨርስቲ አመካኝነት በጥቅምት 30/ 2015 የአንድ ዓመት ውል ተገብቶ እና ለምቶ ለሙከራ ሥራ 13 መ/ቤቶች የሙከራ ስራ ለመጀመር ገና መረጃ የማስገባት ደረጃ ላይ መሆናቸው፣
- የራሳቸውን የተሽከርካሪ ስምሪት የመቆጣጠሪያ ሶፍትዌር ያለሙ፣ በተናጠል የተሽከርካሪዎቻቸውን እና የነዳጅ አጠቃቀም ለመከታተል ለመቆጣጠር ዘመናዊ ጂፒኤስ ለማስገጠም በሂደት ላይ ያሉ መ/ቤቶች መኖራቸው
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የተሽከርካሪ አያያዝ እና የነዳጅ አጠቃቀም ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሥምሪት አስተዳደር (Fleet Management) ሥርዓት ለመዘርጋት በመጀመሪያ የመነሻ (የአዋጭነት) ጥናት ያላደረገ መሆኑ፤
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ለእያንዳንዳቸው ተሽከርካሪዎቻቸው የህይወት ታሪክ መዝገብ /ፋይል እያዘጋጁ መሆኑን እየተከታተለና እያረጋገጠ አለመሆኑና ቅፅ 04 ሳይሞላ (ባዶ) ፋይል እያደረጉት መሆኑ፤ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች የህይወት ታሪክ ፋይል መዝገብ ያልጀመሩ ተቋማት መኖራቸው፣

- የተቀየሩ የተሽከርካሪ ተለዋጭ ዕቃዎች እንደ አዲስ በሞዴል 19 ገቢ የሚያደርጉ እና የተወሰኑትም የራሳቸው ፎርማት ተጠቅመው ገቢ እያደረጉ መሆኑን ባለሥልጣኑ መግለጹ፤
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ዓመታዊ የተሽከርካሪ መረጃዎች የማይልኩ ተቋማት መኖራቸው እና በማይልኩ ተቋማት ላይ ባለሥልጣኑ አስተዳዳራዊ እርምጃ እየወሰደ አለመሆኑ፤
- የተሽከርካሪ ጥገናም እንደማንኛው ግዥ በጨረታ መሆን እንዳለበትና በትልልቅ የተሽከርካሪ አስመጪ ኩባንያዎች በቀጥታ ስምምነት ጥገና በማድረግ የሚወጣውን ወጪ መቀነስ እንዳለበት ቢገለጽም በናሙና የታዩ የፌደራል መ/ቤቶች ብዙዎቹ ባለስልጣኑም ጭምር ከአስመጪ ኩባንያዎች በቀጥታ ግዥ ጥገና እያደረጉ መሆኑ፤
- ባለስልጣኑ እንደ ተቆጣጣሪ መ/ቤት የተሽከርካሪ አያያዝና የነዳጅ አጠቃቀምን አስመልክቶ ዓመታዊ የስልጠና ፍላጎት እየጠየቀና እየሰጠ አለመሆኑ እና የተሽከርካሪ አያያዝና የነዳጅ አጠቃቀምን አስመልክቶ የምክክር መድረክ ተደርጎ የማያውቅ መሆኑን
- በባለስልጣን መ/ቤቱ በመንግስት ተሽከርካሪዎችና የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የውጤታማነት መመዘኛ የዳሰሳ ጥናት አላደረገም፣
- መ/ቤቶች ለ6፣ 7ና ከዛ በላይ ዓመታት ባስለኩት የነዳጅ ኖርማላይዜሽን ልኬት የሚጠቀሙም መኖራቸው፤
- የፌዴራል መንግስቱ አመታዊ የነዳጅ አጠቃቀም ስሌት (ኖርማላይዜሽን) በአመት አንድ ጊዜ ኪ.ሜ. አሰሳ እየተደረገ የሚሰራበት አሰራር የሌለ መሆኑን፣
- በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ ነዳጅ አጠቃቀምና ጥገና መረጃ ልውውጥ የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ፣

ታውቋል፡፡

91. በመሆኑም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሃሣቦች

92. የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን የተሽከርካሪ ስምሪት፣ አያያዝ እና የነዳጅን በአጠቃቀምና አፈፃፀም ዙሪያ የሚሰሩ ስራዎች ውጤት ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ አዋጅ ቁጥር 1333/2016 ለማስፈጸም የተዘጋጀው አዲስ የግዥ መመሪያ በማጸደቅ ወደ ተግባር ሊገባ፣ ለፌዴራል ተቋማትም ስለአፈጻጸሙ ሥልጠናና ግንዛቤ ማስጨበጥ የሚጠበቅበት እና ለአዋጁ አተገባበር የሚያስፈልግ ደንብ ካለም በማርቀቅ እንዲጸድቅ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡
- ሁሉም የፌዴራል ተቋማት ወርሃዊ የተሽከርካሪ ነዳጅ ቅባትና መለዋወጫ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ መላካቸውን ሊያረጋግጥ፣ የማይልኩትን ተቋማት እንዲልኩ ሊያደርግና በማይልኩትም ተቋማት ላይ ተጠያቂነትን የሚያሰፍን አሠራር በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በሙከራ ላይ ያለው የፍሊት ማኔጅመንት በተቻለ ፍጥነት ከሙከራ ደረጃ ወጥቶ በሁሉም የፌዴራል ተቋማት የሚተገበርበትን ስልት በመቀየስ ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በወረቀት ሆነ በሥርዓቱ የሚገኘውን መረጃ በመገምገም ለየተቋማት ግብረ መልስ መስጠትና በግብረ መልሱ መሰረት መፈጸሙን መከታተል ይጠበቅበታል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ሁሉም ተቋማት የበላይ ኃላፊዎች፣ ከፍተኛ ኃላፊዎችና ኃላፊዎች በሚሰጣቸው በሚመደብላቸው ተሽከርካሪ የሚሰጥ ወርሃዊ የነዳጅና ለጥገናቸው የሚወጣ ወጪ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ሪፖርት የሚያደረጉበት፣ የፍሊት ማኔጅመንት ሥርዓት ሲተገበርም መረጃውን ባለሥልጣኑ ተንትኖ ግብረ መልስ የሚሰጥበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል መንግስቱ በየአመቱ ለነዳጅ እና ለጥገና የወጣውን ወጪ አጠቃላይ ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት በሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ለበላይ ኃላፊዎች፣ ለከፍተኛ ኃላፊዎች የሚመደቡ ተሽከርካሪዎች እና የተፈቀደ ነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ በሚኒስትሮች ም/ቤት፣ በጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት እና በገንዘብ ሚኒስቴር በወጡ መመሪያዎችና ሰርኩላሮች ተጠቃለው በሚዘጋጀው መመሪያ ውስጥ መካተታቸውን ሊያረጋግጥና ተግባራዊነታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም አዲሱ የፍሊት ማኔጅመንት ሥርዓት ላይ ለበላይ ኃላፊዎች፣ ለከፍተኛ ኃላፊዎች የሚመደቡ ተሽከርካሪዎች እና

የተፈቀደ ነዳጅ አጠቃቀም በአግባቡ ሊያካትት እና መረጃውንም መሰረት በማድረግ ትንተና ሊሠራና የፖሊሲ ኃሳብ ለሚመለከታቸው አካላት በሪፖርት መልክ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

- ባለስልጣን መ/ቤቱ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ የህጋዊነት ኦዲት በሁሉም የፌዴራል ተቋማት ሊያከናውን ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከሚላክለት ሪፖርቶችና ህጋዊነት ኦዲት ውጤቶች በመነሳት የተገኙ ክፍተቶች የሚሻሻሉበትን መንገድ ተጠሪ ለሆነበት ለገንዘብ ሚኒስቴር አመታዊ ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አገር አቀፍ የሥምሪት አስተዳደር (Fleet Management) ለመዘርጋት ያስለማውን ሶፊት ዌር የሙከራ ትግበራውን በፍጥነት በማጠናቀቅና በሙከራ ትግበራ ወቅት የታዩ ክፍተቶችን በመሙላት በሁሉም የፌዴራል ተቋማት የሚተገበርበትና ስልት በመቀየስና ተገቢውን ሥልጠና በመስጠት በሁሉም ተቋማት ወጥ የሆነ አሠራር እንዲተገበር ሊያደርገ ይገባል፡፡ በፍሊት ማኔጅመንቱ ላይም በሁሉም የፌደራል መ/ቤቶች የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ለእያንዳንዳቸው የህይወት ታሪክ መዝገብ /ፋይል ማስገባት በየጊዜው ወቅታዊ ሊያደርጉና ባለስልጣን መ/ቤቱ ወቅታዊ መሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- የተቀየሩ የተሽከርካሪ ተለዋጭ ዕቃዎች ባለሥልጣኑ ባዘጋጀው ቅጽ ብቻ እየተመዘገቡ ገቢ ስለመደረጋቸው በህጋዊነት ኦዲት ሆነ በክትትል አማካኝነት ሊያረጋግጥ እና ምዝገባውም በሙከራ ትግበራ ላይ ባለው ፍሊት ማኔጅመንት ውስጥ የሚካተትበትን ቅጽ በማካተት ተግባራዊ ሊያደርግና እንደ አዲስ በሞዴል 19 ገቢ እንዳይደረግ ብልሹ አሠራሮችን መከላከል ይጠበቅበታል፡፡
- በባለስልጣን መ/ቤቱ ሁሉም የፌዴራል ተቋማት ያላቸው ተሽከርካሪዎች በሊትር ስንት ኪሎ ሜትር እንደሚሄዱ ሊያስለኩ እና በየአመቱ ልኬቱን ወቅታዊ በማድረግ የነዳጅ አጠቃቀም ኖርማላይዜሽን ልኬት ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በመንግስት ተሽከርካሪዎች አያያዝ፣ ጥገና እናና የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ የፖሊሲ ማሻሻያ ግብዓት ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የኢትዮጵያ ግዥና ንብረት ባለሥልጣን የበላይ ሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች እንዲሁም መረጃ የሰበሰብንባቸው የፌዴራል መ/ቤቶች የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ለኦዲቱ ሥራ መሳካት ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

አባሪ- 1፡ የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)

የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፡- <u>የመንግስት ግዥ እና ንብረት ባላስልጣን</u>

የኦዲቱ አካባቢ፡- <u>የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች የተሽከርካሪ ስምሪት እና የነዳጅ አጠቃቀም አፈፃፀም ውጤታማነቱን መገምገም</u>

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues)	የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)
1. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል ባለበጀት መ/ቤቶች የተሽከርካሪ ስምሪት፣ አያያዝ እና ነዳጅ አጠቃቀምን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ የአሰራር ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፤	1. በባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎች አመዘጋገብ፣ አያያዝ፣ ስምሪት፣ ቁጥጥር እና የነዳጅ አጠቃቀም ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ የአሰራር ሥርዓት ሊዘረጋ እና በየጊዜው ወቅታዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ ፡- ክፍል አንደ፣ ቁጥር 5 እና ገፅ 2 እንዲሁም የፌደራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል 5 ቁጥር 13 .2 ገፅ. 10 እና ሌሎች የተከለሱ ማስረጃዎች ይገባል፡፡
	2. ባለስልጣን መ/ቤቱ በገንዘብ ሚ/ር እና በሌሎች የመንግስት አካላት በተሽከርካሪና ነዳጅ አስተተዳደር ላይ የሚወጡ የህግ ማእቀፎች እና አፈፃፀም ላይ ሀሳብ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ምንጭ፡፡ አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምዕራፍ 2፣ ቁፅር 15 እና አንቀፅ 2
	3. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለተሽከርካሪ ጥገና የተለወጡ እቃዎች በአግባቡ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ መደረጋቸውን የሚከታተልበት ስርዓት ሊዘረጋ እና መተግበሩን ሊከታተል ይገባል፡፡ ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ
	4. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የፌደራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል 2 ቁጥር 7 አንቀጽ1፣ 3፣ ገጽ 4
	5. ባለስልጣን መ/ቤቱ በፌደራል መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም እና የተሽከርካሪ ስምሪትና አያያዝ በተመለከተ ግብረ-መልስ የሚሰጥበት ሥርዓት ሊዘረጋና ሊተገብር ይገባል፡፡ ምንጭ (መልካም ተሞክሮ)
	6. የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች ጥቅም ላይ ውሏል ተብሎ የሚቀርበው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው ኪ.ሜ ጋር እየተመዘገበ እና የቅባት፣የዘይት፣የጥገናና የመለዋወጫ እቃዎች ወጪ በየወሩ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- (የፌደራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪት እና

Office of the Federal Auditor General

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues)	የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)
	አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ገፅ.6 አንቀፅ. 2 እና ከጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር መ 30-899/56 በቀን 16 ነሐሴ 2011 የተላለፈ ሰርኩላር
	7. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎችና ነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ኦዲት ሊያደርግና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- አዋጅ ቁጥር 649/2001 ቁጥር 16 አንቀፅ 4፣ መጋቢት 2014 ዓ.ም የተጠና የዳሰሳ ጥናት ገፅ 204 እና 205፤ የ5 ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ (ከ2013-2017 ዓ.ም) ገፅ 50 እና 51፣
	8. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪ አያያዝ እና አጠቃቀምን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሥምሪት አስተዳደር (Fleet Management ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የ5 ዓመት ስትራቴጂክ. እቅድ (ከ2013 — 2017 ዓ.ም) ገፅ.48፣ መጋቢት 2014 ዳሰሳ ጥናት ገፅ.191
	9. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች ለእያንዳንዳቸው የህይወት ታሪክ መዝገብ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ መዋሉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የፌደራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ 32/2004 ገፅ 3 አንቀፅ 3
	10.ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎችን የነዳጅ መቆጣጠሪያ መኖሩን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡፡ የፌዴራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ገፅ.6 አንቀጥ.1፤ ክፍል 3 ቁጥር 9.1 እና 2፤ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የኦዲት ማከናወኛ ማንዋል ቁጥር 9. 6 ገፅ 110
	11.ባለስልጣን መ/ቤቱ በፌዴራል መ/ቤቶች ለበላይ ኃላፊዎች፣ ለከፍተኛ ኃላፊዎችና ኃላፊዎች በህግ በተፈቀደው መሰረት መመደቡንና ሥራ ላይ መዋሉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- (ከጠቅላይ ሚ/ር ጽሕፈት ቤት በቁጥር መ.30-8991 በቀን ሕዳር 18/2012 የተላለፈ ሰርኩላር ድብዳቤ)፣ በ2009 ዓ.ም በሚኒስትሮች ም/ቤት በተሽከርካሪ አጠቃቀም የወጣ መመሪያ እና በገንዘብ ሚ/ር በ2009 ዓ.ምየተላለፍ ሰርኩላር
	12.ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች ለሚጠቀሚቸው ተሽከርካሪዎች ሙሉ መረጃ አመታዊ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ማቅረባቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የመንግስት ግዥ እና ንብረት ማሻሻያና አቅም ግንባታ መሪ ሥራ አስፈጻሚ የስራ መዘርዝር መግላጫ ገፅ.1፣ መመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል 4 ቁጥር 11.8 እና የተቋሙ ዓመታዊ እቅዶችና

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues)	የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)
	ክንውኖች (2014-2016 በጀት ዓመት)፤
	13.ባለስልጣን መ/ቤቱ በተቀመጠው ገደብ መሰረት ሪፖርት ባላቀረቡ ተቋማት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የመንግስት ግዥ እና ንብረት ማሻሻያና አቅም ግንባታ መሪ ሥራ አስፈጻሚ የስራ መዘርዝር መግለጫ ገፅ.1፣ መመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል 4 ቁጥር 11.8 እና የተቋሙ ዓመታዊ እቅዶችና ክንውኖች (2014-2016 በጀት ዓመት)፤
	14.ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች የተሸከርካሪዎችን የጥገና አገልግሎት ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ መመሪያ ቁጥር 32/2004 ገፅ.7 አንቀፅ 4፣ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የኦዲት ማንዋል ቁፅር 8.10 ገፅ 109
	15.ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎች አጠቃቀም አያያዝና ሥምሪትን በተመለከተ ለመንግስት ተቋማት ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ቁጥር 15 አንቀጽ 3 እና የመኃቢት 2014 ዳሰሳ ጥናት ገፅ 182-183፣ እ10 7
	16.የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎችን ሥምሪትና የነዳጅ አጠቃቀም በተመለከተ በየጊዜው ጥናት ሊያከናውን ይገባል፡፡ ምንጭ፡- አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምእራፍ 2 አንቀጽ 15 ን埦ስ አንቀጽ 13 እና መኃቢት 2014 ጥናት
	17.ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎችና የነዳጅ አጠቃቀም በተመለከተ ተቋማት ሥርዓተ ዘርግተው ተግባራዊ ማድረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡ ምንጭ፡- አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምእራፍ 2 አንቀጽ 15 ንኡስ አንቀጽ 13 እና መኃቢት 2014 ጥናት
2. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መ/ቤቶች የተሽከርካሪ ስምሪት ፣ አያያዝ እና የነዳጅ አጠቃቀምን ቀልጣፋ እና ውጤታማ	18.ባለስልጣን መ/ቤቱ በተሽከርካሪ እና በነዳጅ አጠቃቀም አስተዳደርን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ የቅንጅት ስርዓት ሊዘረጋና ሊተገበር ይገባል፡፡ ምንጭ፡- አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምእራፍ 2 አንቀጽ 15 ንኡስ አንቀጽ 13፣ መኃቢት 2014 የተጠና የዳሰሳ ጥናት ገፅ 182-183፣ 199፣202፣ የ5 ዓመት ስትራቴጂ እቅድ (ከ2013-2017 ዓ.ም) ገፅ 49፣
	19.ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌዴራል የመንግስት ተሽከርካሪና እና ነዳጅ አጠቃቀም የሚያገለግል የመረጃ መለዋወጫና የሚይዙበት ክምችት ማቋቋም፣ ማኅለበት፣መጠበቅና ወቅታዊነቱ የጠበቀ (ውጤታማነት የሚግዝ የመረጃ ስርአት) እንዲሆን እና መደበኛና

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues)	የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)
ለማድረግ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የቅንጅት እና የመረጃ ልውውጥ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱንና መተግበሩን መገምገም፡፡	ጠንካራ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 10 እና መጋቢት 2014 የተጠና የዳሰሳ ጥናት ገፅ 182-183፤ የ5 ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ (ከ2013-2017 ዓ.ም) ገፅ 53 በቁጥር 10.2
	20. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌደራል መንግስት ተሸከርካሪና ነዳጅ አስተዳደር ላይ ሙያን ለማሳደግ ተመሳሳይ ዓላማ እና ተልእኮ ካላቸው በሃገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ለመስራት ጠንካራ ትስስር ሊፈጥር ይገባል፡፡ ምንጭ፡- አዋጅ 649/201 አንቀ. 11፣ 12 እና መጋቢት 2014 የተጠና የዳሰሳ ጥናት ገፅ 183

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General

አባሪ 2: የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ድርጅታዊ መዋቅር



አባሪ. 3 የመንግስት ግዥና ንብረት ማሻሻያና አቅም ግንባታ ስራ አስፈጻሚ ተግባር እና ኃላፊነት

የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 649/2001 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት በተዋረድ ለስራ አስፈጻሚው የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

- የመሪ ስራ አስፈጻሚ ስራዎች ማቀድ፣ መምራት፣ ማስተባበር፤
- የመንግስት ግዥና ንብረት አሰራሮችን መዘርጋት፣ ማስተባበር፣ መምራት፤
- የመንግስት ግዥና ንብረት አቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ማመቻቸት፣ ስልጠና እንዲሰጡ ማድረግ እና ማረጋገጥ፤
- የመንግስት ግዥና ንብረት ልዩ ፊቃድና የምክር ጥያቄዎችን እንዲመረመሩና ውሳኔ እንዲሰጣቸው ማድረግ፣ ማስተባበር፣ መምራት፤
- ሃገራዊ የመንግስት ግዥና ንብረት ዕቅዶችን እንዲዘጋጁ ማድረግ፣ ማስተባበር፣ መምራት
- ባለቤት የሌላቸው ንብረቶች በአግባቡ እንዲያዙ፣ እንዲተዳደሩና እንዲተላለፉ ማድረግ፣ ማስተባበር፣ መምራት፤
- ግዥና ንብረት መረጃዎችን እንዲተነተኑና እንዲሰራጩ ማድረግ፣ ማስተባበር፣ መምራት
- ግዥና ንብረት አስተዳደር አፈፃፀሞችን በክትትልና ቁጥጥር ማረጋገጥ የሚሉ ናቸው፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General

አባሪ.4 በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ የፌደራል መ/ቤቶች ለበላይና ለከፍተኛ ኃላፊዎች ተሽከርካሪና ነዳጅ ከተፈቀደላቸው ውጪ የተመደበ ስለመሆኑ የሚያሳዩ 3 ሰንጠረዦች፡-

1. **ለሚንስትሮችና ለሚንስትር ዴኤታዎች የተፈቀደው ተሽከርካሪ 2 (ለራሳቸውና ለቤተስብ) በአይነትም አውቶሞቢል በሆንም ከተፈቀደው በላይ እና በአይነትም አውቶሞቢል መኪና እየተጠቀሙ አለመሆኑን የሚቀጥለው ሰንጠረዥ ይመልከቱ፡**

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	ለሚንስትሩ የተመደበ የተሽከርካሪ		ለሚንስትር ዴኤታ የተመደበ የተሽከርካሪ		ምርመራ
		ብዛት	አይነት	ብዛት	አይነት	
1.	ትምህርት ሚ/ር	2	ቶዮታ v6L	2	ቶዮታ v6L	
			አውቶሞቢል		ቶዮታ ላ/ክሮዘር	
				2	ቶዮታ v6L	
					ራቫ 4	
2.	ገንዘብ ሚ/ር	4	አውቶ-ሞቢል	5	አውቶሞቢል	
			V-8 ቶዮታ		ቶዮታ ደብል ፒክአፕ	
					V8	
					V8 ቶዮታ	
					ኤሌክትሪክ	
					ለሚ/ር ድኤታዎች ለያንዳንዳቸው 4፣ 4	
3.	ኢንዱስትሪ ሚ/ር	3	ቪ.8	2	ቪ.8	
			ያሪስ		ሌንግዥርን	
			ፐራዶ(መጠባበቂያ)			
				1	ቪ.8	
4.	መስኖእና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር	4	ቪ-6 ቶዮታ	7	ቪ-6 ቶዮታ	
			ቪ-8 ቶዮታ		አውቶሞቢል	
			ቶዮታ ፒክአፕ(ለአጃቢ)		ቪ-8 ቶዮታ	
					ሪቮ ቶዮታ ፒክአፕ	
					ቶዮታ ፒክአፕ	

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

			አውቶሞቢል		ቪ-8 ቶዮታ ቶዮታ ፒክአፕ	
5.	የውሃና ኢነርጂ ሚ/ር	2	ቶዮታ ኮሮላ እና አውቶሞቢል		ቶዮታ፣ እስቴሽዋገን፣ ቪ.8፣	
6.	የከተማና መሰረተ ልማት ሚ/ር	5	ቶዮታ እስቴሽዋገን ቪ.8 ቪ.8 ላንድ ክሮዘር	3	ቶዮታ እስቴሽዋገን ቪ.8 ቶዮታ እስቴሽዋገን ቪ.8 Luxegen Automobil Luxegen Automobil Luxegen Automobil ኒሳን ድርብ ተግባር	
7.	ገቢዎች ሚ/ር	4	ዲኤፌም አውቶሞቢል ቶዮታ ፒክአፕ አውቶሞቢል ቶዮታ ፕራዶ ቶዮታ ቪ.8	4 2	አውቶሞቢል ቪ8 ላንድ ክሮዘር ቪ8 ላንድክሮዘር ቶዮታ ያሪስ አውቶሞቢል አውቶሞቢል ሀርድቶፕ የመስክ ተሽከርካሪ ቶዮታ ቪ.8	
8.	ፍትህ ሚ/ር	3	-ቶዮታ ራሽ፤ ቶዮታ BZ4X፣ -ቶዮታ ቪ.8፣ -ቶዮታ ሀይሉክስ ፒክአፕ(ለሚ/አጃቢ)	3 ሚ/ዴታ1 ሚ/ዴታ2 ሚ/ዴታ3	ቶዮታ ቪ-8፣ -ሌካስንጀን ቶዮታ ቪ-8 ቶዮታ ያሬስ ቶዮታ ቪ-8 ቶዮታ ፒክ-አፕ	

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General

			-ሀይንዳይ -ፎርድ ፒክ-አፕ -ሉክስንጀን -ቶዮታ ሪቫ ቶዮታአውቶሞቢ -ቶዮታ ፎርቹነር -ቶዮታ ፒክ-አፕ	የዘርፍ፡ የጽ/ቤት ኃላፊ፣ የዘርፍ፡ የጽ/ቤት ኃላፊ፣ የዘርፍ፡ የጽ/ቤት ኃላፊ፣ 5 በደፈናው የበላይ ኃላፊ ተበሎ የተገለፁ	-ሉካስንጀን -ቶዮታ ሪቫ-4 -ቶዮታ ሃይሎክስ -ቶዮታ ቨ-8፣ -ቶዮታ ቨ-8፣ ቶዮታ ቨ-8 ቶዮታ ላንድ ክሩዘር ቶዮታ ቨ-8	
9.	ጤና ሚ/ር	---	---	---	---	በተደጋጋሚ የተሽከርካሪ ዝርዝር ማስረጃ ለኦዲት ስራ አልቀረበም የቼክሊስት/ ዝርዝር ማስረጃ አልተሞላም
10	ማዕድን ሚ/ር	5 የሚ/ር ጽ/ቤት ተብሎ እንጂ ለሚኒስትሩና ለቤተሰብ ተብሎ በግልፅ አልተቀመጠም	ፎርቹነር፣ አውቶ-ሞቢል፣ ቪ-8፣ ፒክ-አፕ፣ ፎርቹነር፣	በዲኤታዎቹ የሚ/ር ጽ/ቤት ተብሎ የተገለፁ 6 ተሽከ. ተብሎ እንጂ ለሚኒስትሩና ለቤተሰብ ተብሎ በግልፅ አልተቀመጠም	ራቫ-4 ቪ-8 ፒክ-አፕ ፕራዶ ፎርቹነር ቪ-8	

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General

<u>በዋና ዳይሬክተር ደረጃ የሚመሩ መ/ቤቶች ለዋና ዳይሬክቶርና ለምክትል ዋና ዳይሬክቶር የተፈቀደላቸው አንድ አንድ በአይነትም አውቶሞቢል መኪና ቢሆንም ሁለትና ከሁለት በላይ እና የፊልድ መኪና እየተጠቀሙ መሆኑን ለማሳየት የሚቀጥለው ሰንጠረገዥ ይመልከቱ፡</u>

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	ለዋና ዳይሬክተር (ዋና ስራ አስኪያጅ) የተመደበ የተሽከርካሪ		ለም/ዋና ዳይሬክተር የተመደበ የተሽከርካሪ		ምርመራ
		ብዛት	አይነት	ብዛት	አይነት	
1.	ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት	2	FORD D/CABIN Toyota S/wagen	2	Toyota S/wagen v8 Toyota d/cabin	
2.	የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን	2	ቶዮታ ፒራዶ ቶዮታ ፒራዶ	2	ቶዮታ ፒራዶ ዲኤፌም	
3.	አለርት ሆስፒታል	2 1	ፒክአፕ ቻይና ዶንግፌንግ አውቶሞቢል፤ ቶዮታ-ድርብ ግንባር (ፒክ-አፕ) ዋ/ዳይሬክቶር ጽ/ቤት ኃላፊ	1	ቶያታ-ድርብ ግንባር(ፒክ-አፕ)	
4.	ቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል	1	----	1	---	
5.	ግብርና ባለስልጣን	---	---	---	---	በተደጋጋሚ በተላከላቸው ቼክሊስት ሞልተው እንዲላክ ቢጠየቅም የተሸከርካሪ ዝርዝር ማስረጃ አላኩም፤ በቃለ-መጠይቁም አልተገለፀም
6.	የእንስሳት ልማት እንስትቱት	3	2 ላንድ ክሩዘር 1 ራቫፎር	2	ላንድ ክሩዘር አውቶ-ሞቢል	
7.	የሂሳብ አያያዝ ኦዲት ቦርድ	1	ሚስቲቡሽ ፓጃሮ	1	ደ.ፈ.መ ዋዝ አውቶሞቢል	ለ2ቱ ተጠባባቂ 1 ቶያታ ፒክ አፕ አለ አጠቃላይ 3

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General

8.	ማእከላዊ ስታትክስ	---	Dongfeng Automobile	5	TOYOTA V -8 TOYOTA V -8 TOYOTA V -8 Dongfeng Automobile Dongfeng Automobile የ2ት ም/ዋ/ዳ	ዋና ዳይሬክቶሩ ቀድሞ ከነበሩበት መ/ቤት ይዘዉት የመጡ አንድ መኪና አለ እንጂ
9.	ፀረሙስና ኮሚሽን	3	---	3	---	የተሽከርካሪዎች አይነት አልተገለፀም

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

ለዩኒቨርሲቲዎች ለፕረዚዳንትና ለምክትል ፕረዚዳንት የተፈቀደላቸው አንድ አንድ በአይነትም አውቶሞቢል መኪና ቢሆንም ሁለትና ከሁለት በላይ እና የፍልድ መኪኖች እየተጠቀሙ መሆኑን ለማሳየት የሚቀጥለው ሰንጠረዦች ይመልከቱ፡-

ተ.ቁ	የዩኒቨርሲቲው ስም	ለህላፊዎች የተመደበ የተሽከርካሪ		ለም/ሀላፊዎች የተመደበ የተሽከርካሪ		ምርመራ
		ብዛት	አይነት	ብዛት	አይነት	
1.	አዳማ ዩኒቨርሲቲ	5	ቶዮታ እስቴሽዋገን ቶዮታ ላንድክሮዘር ቶዮታ ፕራዶ ሀዩንዳይ ሚትስቡሽ ፓጀሮ	---	---	
2.	ቦረና ዩኒቨርሲቲ	2	ቶዮታ ሀይሉክስ ቶዮታ ሀይሉክስ	3	ቶዮታ ሀይሉክስ ቶዮታ ሀይሉክስ ቶዮታ ላንድ ክሮዘር ማርክ 2	
3.	ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ	6	ቶዮታ ኮብራ ላንድክሮዘር ፕራዶ ኮብራ ቶዮታ ቶዮታ ላንድክሮዘር ስቴሽዋገን/ቶዮታ ዳፐልካቢንፒክአፕ ቢሾፍቱ ፒክአፕ	---	---	
4.	እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ	4	ላንድክሮሰር ላንድክሮሰር HH 2 ፒክአፕ SANDSTORM	2	FUTON አባዱላ FUTON አባዱላ	
5.	ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ	2	ሃርድቶፕ ሃርድቶፕ	---	---	
6.	ጅማ ዩኒቨርሲቲ	1	ኮሮላ	2	ኮሮላ ኮሮላ	

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General

7.	ጂንካ ዩኒቨርሲቲ	1	ሚስትቡሽ ፓጃሮ	---	---	
8.	መቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲ	2	የመስክ መኪና ድርብ ተግባር	3	ድርብ ተግባር ድርብ ተግባር ድርብ ተግባር	
9.	ጂጂጋ ዩኒቨርሲቲ	-	በተደጋጋሚ በተላከላቸው ቼክሊስት እንዲላክ ቢጠየቅም የተሽከርካሪ ዝርዝር ማስረጃ አልተላከም፡፡ ነገር ግን ከአጠቃላይ (52) 24ቱ የጋራ ተብሎ የተገለፀ በመሆኑ 28ቱ የሃላፊዎች መሆናቸው ነው	---	---	በተደጋጋሚ በተላከላቸው ቼክሊስት እንዲላክ ቢጠየቅም የተሽከርካሪ ዝርዝር ማስረጃ አልተላከም፡፡ ከአጠቃላይ (52) 24ቱ የጋራ ተብሎ የተገለፀ በመሆኑ 28ቱ የሃላፊዎች መሆናቸው ነው
10.	አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ	---	---	---	---	የተሽከርካሪ ዝርዝር ማስረጃ አልቀረበም፡፡
11.	አምቦ ዩኒቨርሲቲ	4	የመስክ ተሽከርካሪዎች	5	የመስክ ተሽከርካሪዎች፣ ለመካከለኛ ሃላፊዎች 10 ፒክ አፕ	
12.	መቀለ ዩኒቨርሲቲ	1 1	--- (የፕ/ጽ/ቤት)	1	---	አጠቃላይ የኃላፊ ተብሎ 3 ተሽከርካሪ ተገልፀዋል
13.	ወራቤ ዩኒቨርሲቲ	1 1	ሃርድቶፕ ፒክአፕ ደብል (ለፕ/ጽ/ቤት)	1	ሃርድቶፕ	
14.	ወልቅጤ ዩኒቨርሲቲ	---	ቼክሊስቱ ሞልተን /የተሽከርካሪ መረጃ ልከናል ቢሉም ኦዲት ቡድኑ ጋ አልደረሰንም	---	---	
15.	ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ	9	9 (ዘጠኝ) ተሽከርካሪ	---	---	9 (ዘጠኝ) ተሽከርካሪ

			ለኃላፊዎች ተብሎ ነው የተገለፀው			ለኃላፊዎች ተብሎ ነው የተገለፀው
16.	ራያ ዩኒቨርሲቲ	1 1	--- 1 (የፕ/ጽ/ቤት)	1	---	ለኃላፊዎች 3 ተብሎ ነው የተገለፀው (የፕ/ጽ/ቤት)
17. ሶ	አሶሳ ዩኒቨርሲቲ	3	ፓጃሮ ሳንድስቶርም 1 ሃይሎክስ (ለፕ/ጽ/ቤት)	3	ሃርድቶፕ ሃርድቶፕ ሃይሎክስ	ለዳይሬክቶሬቶችም፡- 3 ሃርድቶፕ እና 1 ሃይሮፊክ ለዲን 4 ኒሳን ለአዲስ አበባ ጽ/ቤት
18.	ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ	---	----	---	---	በተደጋጋሚ በተላከላቸው ቼክሊስት እንዲላክ ቢጠየቅም የተሽከርካሪ ዝርዝር ማስረጃ አላኩም፤ በቃለ-መጠይቁም ዳሽ አድርገዉታል
19.	ሓረማያ ዩኒቨርሲቲ	---	---	---	---	በተደጋጋሚ በተላከላቸው ቼክሊስት መልቶ እንዲልኩ ቢጠየቅም የተሽከርካሪ ዝርዝር ማስረጃ አላኩም እንዲሁም በቃለ-መጠይቁም አልተገለፀም
20.	ሰመራ ዩኒቨርሲቲ	3 ለፕረዝዳንት ጸ/ቤት	ፓራዶ፣ ፓጃሮ፣ ሃይሩፍ	3	ሪቮ ፒክ-አፕ (ለከፍተኛ ኃላፊ)፣ ፓራዶ (ለከፍተኛ ኃላፊ)፣ ሃርድቶፕ (የመስክ) (ለከፍተኛ ኃላፊ)፣	
21.	አክሱም ዩኒቨርሲቲ	---	የተሽከርካሪ መረጃ ልከናል ቢሉም መኪናው ዋና ጊቢ (ውጪ) መሆኑ እንጂ ማን	---	---	

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

			እንደያዘው አያሳይም			
22.	ጎንደር ዩኒቨርሲቲ	---	---	---	---	በተደጋጋሚ፡በተላከላቸው ቼክሊስት መልቶ እንዲልኩ ቢጠየቅም የተሸከርካሪ ዝርዝር ማስረጃ አላኩም፤ በቃለ-መጠይቁም አልተገለፀም ዓመታዊ አይላክም
23.	ዲሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ	2	ፓጀሮ ፓካፕ	ለአካዳሚክ ለም/ፕዝ IOT ለቴኪኖሎጂ ሽግግር ፕረዝዳንት	- ላንዲክዘር - ፓካፕ - ላንዲክዘር - ላንዲክዘር - ፓካፕ	
24.	ወሎ ዩኒቨርሲቲ	1	ፓጀሮ	V.Presidant:RCS V.P፡ AVP፡ CED፡ SD፡	ማዝዳ፣ ሃይሎክስ፣ ሃርድቶፕ፣ ማዝዳ፣ ላንዲክዘር	
25.	አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ		በተደጋጋሚ የተላከላቸው ቃለ-መጠይቅና ቼክሊስት ሞልቶ ማስረጃ አስደግፎ እንዲላክ ቢጠየቁም እንልካለን እያሉ የቆዩ ቢሆንም ሳይልኩ ቀርቷል፡፡			በተደጋጋሚ በተላከላቸው ቼክሊስት እንዲላክ ቢጠየቅም የተሸከርካሪ ዝርዝር ማስረጃ አላኩም
26.	አርሲ ዩኒቨርሲቲ		በተደጋጋሚ የተላከላቸው ቃለ-መጠይቅና ቼክሊስት ሞልቶ ማስረጃ አስደግፎ እንዲላክ ቢጠየቁም እንልካለን እያሉ የቆዩ ቢሆንም ሳይልኩ			

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

			ቀርቷል፡፡			
27.	ወለጋ ዩኒቨርሲቲ		በተደጋጋሚ የተላከላቸው ቃለ-መጠይቅና ቼክሊስት ሞልቶ ማስረጃ አስደግፎ እንዲላክ ቢጠየቁም እንልካለን እያሉ የቆዩ ቢሆንም ሳይልኩ ቀርቷል፡፡			
28.	አዋሳ ዩኒቨርሲቲ		በተደጋጋሚ የተላከላቸው ቃለ-መጠይቅና ቼክሊስት ሞልቶ ማስረጃ አስደግፎ እንዲላክ ቢጠየቁም እንልካለን እያሉ የቆዩ ቢሆንም ሳይልኩ ቀርቷል፡፡			

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General

አባሪ.5 ለባለሥልጣኑ መረጃ የማይልኩና የኖራማላይዜሽን ልኬት የሚያከናውኑ ተቋማት

ከ169 የፌደራል መ/ቤቶች፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ ወደ 50 የሚሆኑ መ/ቤቶች የነዳጅና ጥገና ወርሃዊ ሪፖርት በከፊል የሚልኩና የማይልኩ እና ዓመታዊ ተሽከርካሪ መረጃ የማይልኩ፣ የተሽከርካሪዎቻቸው ኖርማላይዘሽናቸው ከ2 በተለይ 3 ዓመት በላይ ሆኖ ያላሳደሱ፣ በቀጥታ በአስመጪዎች የሚያስጠግኑ ተቋማት መኖራቸው ለማሳየት እንዲሁም በናሙና ውስጥ ያልተካተቱ ነገር ግን የነዳጅና ጥገና ወርሃዊ ሪፖርት በከፊል የላኩ መ/ቤቶች የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡፡

- ❖ 95 የሚሆኑ መ/ቤቶች የነዳጅና ጥገና ወርሃዊ ሪፖርት እና ዓመታዊ ተሽከርካሪ መረጃ ከማይልኩ (በቀረበልን ማስረጃ መላካቸው የሚያሳይ ማስረጃ ያልተገኘ መሆኑ) ታውቋል፡፡

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	የጥገና ወጪያቸው ከፍተኛ የሆነ፣ ድግግሞች ካለ ከ2014 እስከ 2017 2ኛ ሩብ ዓመት	ወርሀዊ ሪፖርት እና አመታዊ የተሽከርካሪ መረጃ <u>የማይልኩ</u> (ለምሳሌ 4 ጊዜ ከለኩ 4 ይባላል በዓመቱ ስር ማለት ነው፡፡				ዓመታዊ የተሽከርካሪ መረጃ ሪፖርት (ከ2014-2016)	ኖርማላይዜሽን ልኬታቸው ሁለት አመት ያለፈው	በቀጥታ በአስመጪዎች ወይም በቀጥታ ግዥ የሚያስጠግኑ
			2014	2015	2016	2017			
1.	ግብርና ባለስልጣን	የጥገና ወጪ ከፍተኛ	የለም	የ 8 ወር የተለከ	የ 7 ወር ተላከ	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	ማስረጃው አልቀረበም	ማስረጃው አልቀረበም
2.	ትምህርት ሚ/ር	በዓመት የጥገና ድግግሞሽ አለ የጥገና ወጪ ከፍተኛ	የለም	የ 6ወር የተላከ	የ 6ወር የተላከ	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	የ 2015 ዓ.ም ልኬት ነው	በቀጥታ ከአስመጪዎች እና -ከፐብሊክ ትራንስፖርት አገልግሎት ውል በመግባት
3.	የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት	በ2015 ዓ.ም የጥገና ወጪ ከፍተኛ	የለም	የ 6ወር የተላከ	የ 6ወር የተላከ	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	የ 2015 ዓ.ም ልኬት ነው	ከአፍሪካ ሌክሲ እና ከአስመጪዎች ውል በመግባት እና በቀጥታ በአስመጪዎች የሚጠገን
4.	ገቢዎች ሚ/ር	የጥገና	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ.ዓመት	የ2015ዓ.ም ልክት፡	ገነት ገራዥ በቀጥታ

		ድግግሞች አለ					የለም	፡ በኮሚቴም ያስለካሉ	ግዥ
5.	የኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ		የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ.ዓመትየ ለም		በቀጥታ ከአስመጪዎች ብቻ የሚጠገን
6.	ገንዘብ ሚ/ር	ማስረጃው አልቀረበም	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	(የ2012 ዓ.ም) ልኬት ነው ወደ 6 አከባቢ ሆኖታል	በቀጥታ ከአስመጪዎች እና በራሳቸው ጋራዥ የሚጠገን
7.	ጂጂጋ ዩኒቨርሲቲ	ድግግሞችና ከፍተኛ ወጪ አለ	የ12 ወር ተልኳል	የ 10 ወር ተልኳል	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት አልላከም /የለም	የ2014ዓ.ም ልኬት ነው ከ3 ዓመት አከባቢ በኮሚቴ	
8.	መቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልቀረበም	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም		በቀጥታ ከካፐፓኒዎች የሚጠገን
9.	አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልቀረበም	የለም	የ2015ዓ.ም በሶፊት ኮፒ ነው መላኩ አይታወቅም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት አልላከም /የለም	የ2013ዓ.ም ልኬት ነው 4 ዓመት ከ6ወር	በራሳቸው ገራዥ እና በአስመጪ ካምፓኒዎች
10.	መስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር	ማስረጃው አልቀረበም	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም		ኢትዮጲያስራዎች ኮርፖሬሽን በቀጥታ እና በቀጥጣ ከካምፓኒ የሚጠገን
11.	ከተማና መሰረተ ልማት ሚ/ር	የጥገና ከፍተኛ ወጪ	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት አልላከም /የለም		በቀጥታ ግዥ ከፌዴራል ቤቶች ሰርቪስ ጥገና ይደረጋል
12.	ፀረ-ሙስና ኮሚሽን	ማስረጃው አልቀረበም	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት አልላከም /የለም	ማስረጃው አልቀረበም	በቀጥታ ከአስመጪዎች ጥገና ይደረጋል
13.	ቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል		የለም ነው	የለም	የ 9 ወር ሓለ	የለም	የ3ቱ ዓመት አልላከም /የለም	በ2015 ዓ.ም በኮሚቴ የተለካ	በራሳቸው መካኒክ እና ከስመጪዎች በቀጥታ የሚጠገን
14.	ኢንዱስትሪ ሚ/ር	የጥገና ድግግሞች	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	የ2015 ዓ.ም	በቀጥታ ከካምፓኒ የሚጠገን

		አለ							
15.	ጤና ሚ/ር	ማስረጃው አልቀረበም	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለ	ማስረጃው አልቀረበም	
16.	ፍትህ ሚ/ር	የጥገና.ድግግሞች አለ	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም		ቀጥታና በጨረታ ከጆኒ ገራዥ እና ከአስመጪዎች
17.	ግብርና ምርምር		የለም	የለም	የ 3 ወር ተልኳል	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	የ2013 ዓ.ም ሊኬት ነው	
18.	የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን		የለም	የ 7 ወር ተልኳል	የ 7 ወር ተልኳል	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም		ከአስመጪዎች ነው፣ የውል ስምምነት አልቀረበም
19.	የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት	ማስረጃው አልተላከም	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	ማስረጃው አልተላከም	ማስረጃው አልተላከም
20.	መዕድን ሚ/ር	ማስረጃው አልተላከም	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	ማስረጃው አልተላከም	ማስረጃው አልተላከም
21.	መቀለ ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልተላከም	ከ2014 ዓ.ም በፊት አለ	የለም	የለም	የለም	ከ2014 ዓ.ም በፊት አለ	የ2014 ዓ.ም ሊኬት ነው	ከግል ጋራዥ የውል ስምምነት አላቸው
22.	ሓረማያ ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልተላከም	የለም	የ 11 ወር ተልኳል	የ 4 ወር ተልኳል	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	ማስረጃው አልተላከም	ማስረጃው አልተላከም
23.	በህርዳር ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልተላከም	የ 2 ወር ተልኳል	የ 10 ወር ተልኳል	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	ማስረጃው አልተላከም	ማስረጃው አልተላከም
24.	ጅማ ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልተላከም	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	ማስረጃው አልተላከም	ማስረጃው አልተላከም
25.	ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልተላከም	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	ማስረጃው አልተላከም (የለም)	-በሰርቪስ ወቅት አንድ ላይ በአስመጪዎች(ሞይከ) በቀጥታ የጠገናሉ፤ -ከሌላ ጋራዥ ውል አለን ቢሉም ማስረጃው አልተላከም
26.	ቦረና ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልተላከም	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	ማስረጃው አልተላከም	ማስረጃው አልተላከም

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት Office of the Federal Auditor General

27.	ራያ ዩኒቨርሲቲ		የለም	የለም	የለም	የለም	በየዓመቱ እንደሚላክ ግን ማስረጃው አልተገኘም		የራሳቸው ገራዥ እና ከሌላም ውል አላቸው
28.	መቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልተላከም	የ2013 ዓ.ም ከተሽከርካሪ መረጃ ጋ የተላከ	የለም	የለም	የለም	የ3ት ዓመት ልከናል ብለዋል ግን የ2013 ዓ.ም ብቻ ነው የተገኘው		ከአስመጪዎቹ በቀጥታ
29.	አክሱም ዩኒቨርሲቲ		የለም	አለ ግን ስለመላኩ ደብዳቤው አልተያያዘም	የለም	የለም	ማስረጃው አለቀረበም	የለረኬቱ ዓመት አልተገለፀም	
30.	ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልተላከም	የ 1 ወር	የ 12 ወር ተልኳል	የ 6 ወር ተልኳል	የለም	የ2014 ብቻ	ሊኬቱ በባለሙያዎች የተለካ ሲሆን ዓመቱ አልተገለፀም	ቀጥታ ከአስመጪዎቹ በየ20000ኪ.ሜ ሰርቪስና ጥገና
31.	እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልተላከም	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	ማስረጃው አልተላከም	ከአስመጪዎቹ በቀጥታ እና አንስተኛ ጥገና ከግል በጨረታ
32.	ወራቤ ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልተላከም	የለም	የለም	የለም	የለም	አለ ቢሉም ማስረጃው አለቀረበም	የ2012 ዓ.ም ሊኬት ነው	ማስረጃው አልተላከም
33.	ጎንደር ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልተላከም	የ11 ወር ተልኳል	የ 10 ወር ተልኳል	የለም	የ 1 ወር ብቻ	የ3ቱ ዓመት የለም	ማስረጃው አልተላከም	ማስረጃው አልተላከም
34.	አዳማ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልተላከም	የለም	የ 5 ወር ተልኳል	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	ማስረጃው አልተላከም	ማስረጃው አልተላከም
35.	ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልተላከም	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	ማስረጃው አልተላከም	ማስረጃው አልተላከም

Office of the Federal Auditor General

36.	ወሎ ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልተላከም	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	ማስረጃው አልተላከም	ማስረጃው አልተላከም
37.	ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልተላከም	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	ማስረጃው አልተላከም	ማስረጃው አልተላከም
38.	ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልተላከም	የለም	የ 6 ወር ተልኳል	የ 4 ወር ተልኳል	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	ማስረጃው አልተላከም	ማስረጃው አልተላከም
39.	አርሲ ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልተላከም	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	ማስረጃው.አልተላከም	ማስረጃው.አልተላከም
40.	አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው አልተላከም	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	ማስረጃው.አልተላከም	ማስረጃው.አልተላከም
41.	ሰላሌ ዩኒቨርሲቲ	ማስረጃው.አልተላከም	የለም	የለም	የለም	የለም	የ3ቱ ዓመት የለም	ማስረጃው.አልተላከም	ማስረጃው.አልተላከም
	በኦዲቱ ወቅት በናሙና ያልታዩ በተወሰነ መልኩ የነዳጅና ጥገና ውርሃዊ ሪፖርት የላኩ መ/ቤቶች								
42.	ህዝብተወካዮች ም/ቤት		የለም	የ11 ወራት የተላከ	የለም	የለም	የለም		
43.	ቤተመንግስት አስተዳደር		የለም	የ 12 ወር የተላከ	የለም	የለም	የለም		
44.	ሰላም ሚ/ር		የለም	የ 12 ወር የተላከ	የለም	የለም	የለም		
45.	የህገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ		የለም	6 ወር የተላከ	የለም	የለም	የለም		
46.	የሲቪል ማህበረሰብ ባለስልጣን			10 ወር የተላከ	ለ7 ወር የተላከ	የለም	የለም		
47.	የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን		የለም	የ 4 ወር ተልኳል	የ 2 ወር ተልኳል	የለም	የለም		
48.	ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን		የለም	የ3 ወር የተላከ	የ 6ወር ተልኳል	የለም	የለም		
49.	እንባ ጠባቂ ተቋም			የ 5 ወር ተልኳል	የ 7 ወር ተልኳል				
50.	የመረጃ መረብ ደህንነት አስተዳደር			የ 6ወር ተልኳል	የ 6ወር ተልኳል				
51.	የውጭ ጉዳይ ሚ/ር			የ 5 ወር					

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

				ተልኳል					
52.	ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን			የ 6 ወር ተልኳል	የ 6 ወር ተልኳል				
53.	ዜና አገልግሎት			የ 6 ወር ተልኳል					
54.	ኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር			የ 3 ወር ተልኳል	የ 6 ወር ተልኳል				
55.	የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን			የ 7 ወር ተልኳል	የ 7 ወር ተልኳል				
56.	ቴክኖሎጂ ባለስልጣን			የ 2 ወር ተልኳል	የ 6 ወር ተልኳል				
57.	የኢትዮጲያ አምሯዊ ባለስልጣን			የ 4 ወር ተልኳል	የ 6 ወር ተልኳል				
58.	የመንግስት ግዥ አገልግሎት			የ 6 ወር ተልኳል	የ 3 ወር ተልኳል				
59.	ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩሽን			የ 4 ወር ተልኳል	የ 7 ወር ተልኳል				
60.	ፖሊሲ ጥናት ተቋም			የ 6 ወር ተልኳል	የ 7 ወር ተልኳል				
61.	ፕላን ኮሚሽን			የ 2 ወር ተልኳል	የ 7 ወር ተልኳል				
62.	አፍሪካ ሊደርሺፕ			የ 3 ወር ተልኳል	የ 6 ወር ተልኳል				
63.	ከስተም ኮሚሽን			የ 12 ወር ተልኳል	የ 4 ወር ተልኳል				
64.	አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን			የ 4 ወር ተልኳል	የ 4 ወር ተልኳለ				
65.	ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚ/ር			የ11 ወር ተልኳል	የ 4 ወር ተልኳል				
66.	ቡናና ሻይ ባለስልጣን			የ5 ወር ተልኳል	የ 5 ወር ተልኳል				
67.	ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክ ሚንስትር			የ 6ወር ተልኳል	የ 5 ወር ተልኳል				

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General

68.	ሲቪልአቬሽን ባለስልጣን			የ 5 ወር ተልኳል	የ 7 ወር ተልኳል				
69.	ኮንስትራክሽን ባለስልጣን			የ5 ወር ተልኳል	የ 7 ወር ተልኳል				
70.	ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ				የ 6 ወር ተልኳል				
71.	ዲላ ዩኒቨርሲቲ			የ 12 ወር ተልኳል					
72.	ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ			የ 6 ወር ተልኳል					

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General

አባሪ .6 ባለስልጣን መ/ቤቱ በፌደራል መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም እና የተሽከርካሪ ስምሪትና አያያዝ ግምገማና ግብረ-መልስ የሚሰጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ ያሉ ክፍተቶች ለማሳያ የሚሆን፡-

- አልፎ አልፎ የበላይ ኃላፊዎች የነዳጅ ወርሃዊ ሪፖርት በሚልኩ ተቋማት ለምሳሌ የኢትዮጵያ አእምራዊ ንብረት ባለስልጣን የምክትል ዋና ዳይሬክተር ተሽከርካሪ የሀምሌ ወር /2015 የተቀዳ ነዳጅ 511 ሊትር ነዳጅ የተቀዳ ሲሆን የጓዘው ኪ.ሜ ያልተገለፀ መሆኑ፣ ታርጋ ቁጥር 4-20345 የመስከረም/2016 ዓ.ም ተሽከርካሪ 370 ሊትር፣ የጥቅምት/2016 ዓ.ም ተሽከርካሪ 547 ሊትር፣ መቀዳቱ፣ የህዳር/2016 ዓ.ም ተሽከርካሪ 300 ሊትር፣ የታህሳስና ጥር/2016 ዓ.ም ተሽከርካሪ 496 ሊትር ቢቀዳለትም በመስክ ስራ ነው አይደለም የሚል ልተገለፀ መሆኑ፤
- የኢትዮጲያ ስታስቲክስ አገልግሎት የታርጋ በህዳር/2016 ዓ.ም ቁጥር 4-11088፣ 4-18684፣ 4-32747፣ 4-25261፣ 4-18683፣ 4-11075፣ 4-15380፣ 4-16168፣ 4-32829፣ 4-15094፣ 4-11100፣ 4-15087፣ 4-26574፣ 4-11077፣ 4-16165፣ 4-18332፣ 4-11096፣ 4-16168 እና በጥር /2016 12 ተሽከርካሪዎች በተመሳሳይ ምንያህል ነዳጅ እንደተቀዳላቸውና ምን ያህል ኪ.ሜ እንደተጓዙ የሚገልጽ ነገር የሌለ መሆኑ፤
- በኢትዮጲያ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን ከሚያዚያ - ግንቦት /2015 የነዳጅ ሪፖርት፡- 4-18787 በ2 ወር 515.95 ሊትር፤ 4-14784 በ 2ወር 863.67 ሊትር፤ 4-22171 በ 2 ወር 992.37፤ 4-14013 በ 2 ወር 768.88፤ 4-17201 በ 2 ወር የተቀዳው ነዳጅ 740.30 ሊትር ሲሆን በመስክ ነው አይደለም የሚል ገለፃ አለመደረጉ፤

❖ የኢትዮጲያ ማሪታይም ባለስልጣን የመጋቢት፣ ግንቦት፣ ሰኔ፣ ሃምሌና ነሃሴ /2015 ዓ.ም የነዳጅ ሪፖርት፡ 4-21084- 576.5 ሊትር እና 354.15.፤ 4-13057 የተቀዳው ነዳጅ 275.76 እንዲሁም 29 ተሽከርካሪዎች እንዳሉት በደብዳቤ ቁጥር ከ70/ማባ88/11/15 በቀን ሀምሌ 5/2015 ዓ.ም ቢያሳውቅም ወርሀዊ የነዳጅ አጠቃቀም ሪፖርት የተላከው የ 7 ተሽከርካሪ ብቻ መሆኑ፤

❖ የስነምግባር እና ሙስና ኮሚሽን ባስጥ ማስታወሻ በ5/2/2016 ከትራንስፖርት ስምሪት ስራ ክፍል ለኮሚሽን ጽ/ቤት ኀላፊ የተፃፈ አለአግባብ ስለተቀዳ ነዳጅ ማለትም ናፍጣ1,398.75 ሊትር ዋጋው 111,550.31 ብር (ለሰሌዳ ቁጥር 4-14624፣ 4-14621፣ 4-14622፣ ፊሪ ካርድ)፤ ቤንዚን 410.18 ሊትር ዋጋው 31,836.5 ብር ለሰሌዳ ቁጥር 4-30608 እና 4-30083 የተቀዳላቸው መሆኑ ይህ የሆነበት ተሽከርካሪዎቹ በጋራዥ ቆሞ እያሉ ባልተፈቀደ መንገድ በቀን ሁለት ጊዜ በመቅዳት በገንዘብ 143, 386.82 ወጪ ተደርጎ እርምጃ ስለመወሰዱ የሚያሳይ ማስረጃ አብሮ ያልተያያዘ መሆኑ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General

❖ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ሚያዚያ፣ ግንቦት፣ ሰኔ፣ ሃምሌ፣ ነሃሴ /2015 ዓ.ም እና ታህሳስና የጥር /2016 የነዳጅ ቅባት እና ዘይት አጠቃቀም 4-24553፣ 426548፣ 4-03123፣ 4-27215፣ 4-23235፣4-23214፣ 4-24552፣ 4-24056፣ 4-26546፣ 4-17161፣ 4-04225 ተሽከርካሪዎች ለኃላፊዎች ተመድበው ነገር ግን አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የከተማና የመስክ ተሽከርካሪዎች መሆናቸው ቢገለፅም በመመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል 3 ተራ ቁጥር 2 መሰረት የነዳጅ ፍጆታቸው ከነምክንቱ /ከነመግለጫው ሪፖርት መደረግ የነበረበት ቢሆንም ያልተካተተ መሆኑን፤

❖ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የሃምሌ/2015 መስከረም፣ ጥቅምት፣ ህዳር፣ ታህሳስ፣ ጥሪ /2016 ዓ.ም የነዳጅ ቅባት እና ዘይት የነዳጅ ቅባት እና ዘይት አጠቃቀም ላ የተሞላ ዘይት፡- የታርጋ ቁጥር 32935 5,200 ሊትር፤ የታርጋ ቁጥር 23273፣ 8,400 ሊትር ሲሆን በዚህ መልኩ 9 ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፤ ታርጋ ቁጥር 35 ዕ/ድ 6394 ሊትር፣ 8,600 ሊትር፤ ታርጋ ቁጥር 4-30473 8,400 ሊትር፤ ታርጋ ቁጥር 4-18778 2,800 ሊትር በዚህ መልኩ 11 ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፤ ታርጋ ቁጥር 4-30618- 6,200 ሊትር፣ ታርጋ ቁጥር 4-29757 - 6,200 ሊትር ሲሆን በዚህ መልኩ 11 ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፤ ታርጋ ቁጥር 4-18778- 8,145 ሊትር፣ 9 ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፤ በጥር/2016 ዓ.ም የታርጋ ቁጥር 4-34841 8,145 ሊትር፣ የታርጋ ቁጥር ዕድ-6394 8,145 ሊትር፣ ታርጋ ቁጥር 4-30618 8,145 ሊትር፤ ታርጋ ቁጥር 4-30473 6,030 ሊትር፣ የታርጋ ቁጥር 4-28924 8,145 ሊትር በዚህ መልኩ 12 ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት Office of the Federal Auditor General

አባሪ..7. የፌዴራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም የሚያገለግሉ ቅጾች ዝርዝር

	የቅጹ ስም	የቅጽ ቁጥር
1	የመንግስት ተሽከርካሪዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች መረከቢያ ቅጽ	ቅጽ 01
2	የመንግሰት ተሽከርካሪዎች ዕለታዊ የነዳጅ፣ የዘይትና የኪ.ሜ. መመዝገቢያ ቅጽ	ቅጽ 02

3	የመንግስት ተሽከርካሪ ወርኃዊ የነዳጅ፣ የዘይትና ጥገና ወጪ ማጠቃለያ ቅጽ	ቅጽ 03
4	የመንግስት ተሽከርካሪዎች የህይወት ታሪክ መመዝገቢያ ቅጽ	ቅጽ 04
5	የመንግስት ተሽከርካሪዎችን ለተጠቃሚው መመደቢያ ቅጽ	ቅጽ 05
6	የመንግስት ተሽከርካሪ መጠየቂያና የመዘዋወሪያ ፈቃድ መስጫ ቅጽ	ቅጽ 06
7	ልዩ መታወቂያ	ቅጽ 07
8	የመንግስት ተሽከርካሪዎች የነዳጅ፣ የዘይትና የቅባት መጠየቂያ ቅጽ	ቅጽ 08
9	የመንግስት ተሽከርካሪዎች የጥገና መጠየቂያ ቅጽ	ቅጽ 09
10	የመንግስት ተሽከርካሪ የጥገና የሥራ ትዕዛዝ ቅጽ	ቅጽ 10
11	የመንግስት ተሽከርካሪ የመለዋወጫ ዕቃ መጠየቂያ ቅጽ	ቅጽ 11
12	በጥገና ወቅት የተለወጡ ዕቃዎች ማቅረቢያ /ሪፖርት ማድረግያ ቅጽ	ቅጽ 12
13	የተሽከርካሪዎች የአደጋ መግለጫ ቅጽ	ቅጽ 13

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General

አባሪ.8. የፍሊት ማናጅመንት በሙከራ ያሉ የፌደራል መ/ቤቶች ዝርዝር

1. ግብርና ሚኒስቴር
2. ገንዘብ ሚኒስቴር
3. ፕላን ሚኒስቴር
4. ጤና ሚኒስቴር
5. የትራንስፖርት ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር
6. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
7. የኢትዮጵያ ስታስቲክስ አገልግሎት

8. የኢትዮጵያመንገዶች አስተዳደር
9. ቅዱስ ጴጥሮስ ስፔሻላዝድ ሆስፒታል
10. የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት
11. የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን
12. ቡናና ሻይ ባለስልጣን
13. የኢትዮጵያ ጠቅላይ አቃቢ ሕግ ናቸው፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General